

Australian Government

# ኣውስትራሊያዊ ዜግነት:

## የጋራ ማስተሳሰሪያችን



ለኣውስትራሊያ ዜግነት ፈተና የሚያስፈልግዎት መረጃዎች ሁሉ ከዚህ መጽሃፍ ውስጥ ያገኛሉ። ይሄንን የዜግነት ፈተና ለማለፍ ሲሉ ሌላ ተጨማሪ ተነባቢ ነገር ከግልም ሆነ ከድርጅት መግዛት ኣያስፈልግዎትም። መምሪያው ለዜግነት ፈተና ሊረዳችሁ ይችላል ብሎ የሚያዘው ሌላ ተነባቢ ነገር ኣይቀበልም ወይም ኣይመክርም።

ኮመንዌልዝ ኣውስትራያ 2020

ከኣውስትራሊያ መንግስት ኣርማ ውጪ በዚህ እትም የተቀመጡት ግብኣቶች ሁሉ በህግ ከተፈቀዱ ቅጅዎች /Creative Commons Attribution 4.0 የተወሰዱ ሲሆን የኣለም ኣቀፉ ፈቃድ በሚመለከትም ቀጥሎ ባለው ድረ ገፅ ላይ ማግኘት ይችላሉ https://creativecommons.org/licenses/by/4.0/legalcode.

ይህም ማለት ፈቃዱን መጠቀም የሚቻለው በሰነዱ ላይ ለሰፈሩት ግብኣቶች ብቻ ነው።

የፈቃዱ ኣጠቃቀም ዝርዝር በተመለከተ በ Creative Commons ድረ ገጽ ላይ https://creativecommons.org/ ይመልከቱ። ይህ ለCC BY 4.0 ሙሉ የህግ ኮድ ስለሆነ ስለ ፈቃዱ የተሟላ መረጃ ለማግኘት https://creativecommons.org/licenses/by/4.0/legalcode ላይ ይመልከቱ።

**የኣርማው ኣጠቃቀም**

ኣርማውን ለመጠቀም ያሉት ዝርዝር ውሎች ቀጥሎ ባለው የጠቅላይ ሚንስቴሩና ካቢኔያቸው ድረ ገጽ ላይ ይመልከቱ https://www.pmc.gov.au/government/commonwealth-coat-arms.

**ያግኙን**

ፈቃዱን በሚመለከትና የዚህ ሰነድ ኣጠቃቀም በሚመለከት ጥያቄ ካልዎት ለመመለስ ቀጥሎ በተመለከተው ኣድራሻ ቢልኩልን ደስተኞች ነን

Portfolio Media and Engagement Branch
Department of Home Affairs
PO Box 25
BELCONNEN ACT 2616

**ማስገንዘቢያ**

የኣቦሪጅናልና ቶረስ ስትሬይት ደሴት ኣንባቢዎች በዚህ እትም ላይ
የሞቱና ወይም ከሞቱ ሰዎች ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ምስል ይታያል

# ማውጫ

ለርስዎ መልእክት 2

## ለፈተና የሚቀርቡ ክፍሎች

ክፍል 1: ኣውስትራሊያና ህዝቧ 7

ክፍል 2: የኣውስትራሊያ ዲሞክራሲያዊ እምነቶች፣ መብቶችና ነፃነቶች 17

ክፍል 3: መንግስትና ህግ በኣውስትራሊያ 23

ክፍል 4: የኣውስትራሊያ እሴቶች 33

ለፈተና የሚቀርቡ ክፍሎች የሚያግዝ የቃላት መፍቻ 40

## ለፈተና የማይቀርቡ ጥያቄዎች

ክፍል 5: ኣውስትራሊያ ዛሬ 48

ክፍል 6: የኣውስትራሊያችን ታሪክ 63

ለፈተና የማይቀርቡ ክፍሎች የሚያግዝ የቃላት መፍቻ 84

ለተጨማሪ መረጃ 86

ምስጋናዎች 88

# ለርስዎ መልእክት

የኣውስትራሊያ ዜጋ ለመሆን በመምረጥዎ እንኳን ደስ ኣልዎት። በኣንድ ኣዲስ ኣገር ለመኖርና እንደ ሙሉ ዜጋ ለመሳተፍ መቻል ከፍተኛ ጉብዝና፣ ጥረትና ቁርጠኝነት ያስፈልጋል። ለሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ማህበረሰባችን የሚያበረክቱት ኣስተዋፅኦ ትልቅ ዋጋ እንሰጣለን።

የኣውስትራሊያ ዜግነት በስደት ታሪክዎ ኣንድ ጠቃሚ ምዕራፍ ነው። ኣውስትራሊያዊ ዜጋ መሆን ማለት ለኣውስትራሊያና የጋራ እሴቶችዋ በቀጣይነት ኣስተዋፅኦ ለማድረግ ቃል መግባት ነው። የኣውስትራሊያ መደበኛ የማህበረሰብ ኣባል መሆን የሚጀምሩበት ማለትም ነው። “እኔ ኣውስትራሊያዊ ነኝ” ለማለት የሚያስችልዎ ደረጃ ነው።

የኣውስትራሊያ ዜግነት ብዙ ፀጋዎችና ሽልማቶች የሚያስገኝ ልዩ መብት ነው። የኣውስትራሊያ ዜጋ በመሆንዎ፣ ወደ ኣንድ ልዩ ብሄራዊ ማህበረሰብ እየተቀላቀሉ ነው። ሃገራችን የተገነባችው በመጀመሪያ ነዋሪ በሆኑ ኣቦርጅኖችና በቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች/Aboriginal and Torres Strait Islander peoples ህዝቦች፣ በውርስ ካገኘናቸው ዲሞክራቲክ ከሆኑ የብሪቴይን ተቋማት እና ከመላው ዓለም ከመጡ ስደተኞች አስተዋፅዖ ነው። ይህንን ብዝሃነታችንን እናከብራለን፤ በሌላ በኩል ደግሞ የተባበረችና ስምምነት ያላት ሃገር ለመገንባት ጥረት እናደርጋለን።

የኣውስትራሊያ ማህበረሰብ ጥንካሬ የሚመነጨው ችግሮችን ለመፍታት ኣብሮ በመስራት የኣውስትራሊያን የወደፊት ተስፋ ቅርፅ በማስያዝ ነው። በጣም የተረጋጋ ስርዓተ መንግስት ኣለን፤ በተጨማሪም ኣውስትራሊያውያን የመንግስት ስልጣንና ህገ መንግስትን እናከብራለን። መረጋጋታችን፣ ባህላችንና ህጋችን በታሪካችን የተቀረፁ ናቸው። የኣውስትራሊያ ማህበረሰብ በመቀላቀልዎ በኣውስትራሊያ ታሪክ ላይ እየጨመሩ ሃገሪቷን በማነፅ ሂደት የራስዎን ኣስተዋፅኦ ያደርጋሉ።

ኣውስትራሊያ ጥንታዊ ምድር ናት። ሰፊና ልዩም ናት። የዝናባማ ደኖች፣ የእንጨት መሬቶች፣ የባህር ዳርቻዎች፣ የምድረ-በዳዎች፣ የከተሞችና የግብርና ኣገር ናት። ሃገር በቀል ታሪኮቻችን በጥንታዊነታቸው በዓለም ደረጃ ኣስካሁን ተወዳዳሪ የሌላቸውና ሳያቋርጡ እስካሁን የዘለቁ ባህሎች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ኣዲስና ታዳጊ ኣገር፤ የመጤዎች/የስደተኞች ኣገር ነን። የኣውሮፓ ሰፋሪዎች በኣውስትራሊያ በ1788 የተጀመረ ሲሆን ኣሁንም ቢሆን ሌሎች መጤዎችን መቀበላችን ቀጥለናል።
ኣውስትራሊያን ኣሁን ከ200 ሃገሮች በላይ የመጡ ሰዎች ቤታቸው ኣድርገዋታል። በዚህም ምክንያት ማህበረሰባችን በዓለም ደረጃ ከፍተኛ የህዝብ ስብጥር ካላቸው የዓለም ማህበረሰብ ኣንዷናት። ኣውስትራሊያ የተለያዩ ብሄሮችና ባህሎች ልዩነትና ሃገራዊ ኣንድነት በተሳካ መልኩ ኣዋህዳ የቀጠለች ኣገር ናት። ዜግነታችን ሁላችንም የሚያስተሳስረን የጋራ ሰንሰለት ነው።
ኣውስትራሊያ በዲሞክራሲ የምትመራ ኣገር ናት። ዜግነትዎ ይቺን ሃገር በዲሞክራሲያዊ መንገድ ለመገንባት ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖርዎት የሚያስችል እድል ይሰጥዎታል። ይህም ማለት እንደ ማንኛውም ኣውስትራሊያዊ የማህበረሰብ ኣባል ሃላፊነትዎን ለመወጣት ዝግጁ ያደርግዎታል ማለት ነው።
ኣውስትራሊያውያን በሰዎች ክብርና ነፃነት፣ በወንድና ሴት እኩልነት እንዲሁም በህግ የበላይነት የመሳሰሉ የጋራ እሴቶችን እናምናለን። ኣውስትራሊያዊ ዜግነት ማለት እነዚህን የጋራ እሴቶች የዕለት ተለት ኑሮ ኣድርጎ መኖር ማለት ነው።

# የኣውስትራሊያ ዜጋ መሆን

የኣውስትራሊያ ዜጋ መሆን ማለት ኣንድ ሰው ለኣውስትራሊያና ለህዝቧ ታማኝ ለመሆንና እንደ ሃገሪቱ ዜጋም መብቱና ግዴታውን ኣክብሮ ለመኖር ቃል የሚገባበት ኣንድ ጠቃሚ ሂደት ነው።

## የኣውስትራሊያ የዜግነት ፈተና

የኣውስትራሊያ የዜግነት ፈተና የተዘጋጀው እርስዎ ስለ ኣውስትራሊያ፣ ስለዲሞክራሲ ስርዓቷ፣ ስለጥቅሟና እሴቶቿ፣ እንዲሁም የዜግነት ሃላፊነትና መብቶች በቂ እውቀት ያገኙ መሆን ኣለመሆንዎን ለመመዘን ነው።

የዜግነት ፈተና የሚካሄደው በኮምፒዩተር ሲሆን ፈተናውም በእንግሊዝኛ የተዘጋጁ የምርጫ ጥያቄዎችን የያዘ ነው። ፈተናው የሚያካትተው 20 በዘፈቀደ የተመረጡ ጥያቄዎች ሲሆኑ ከህዳር 15 ቀን 2020 ዓ/ም ጀምሮ ኣምስቱ ጥያቄዎች ስለ ኣውስትራሊያ እሴቶች የሚያተኩሩ ናቸው።

ፈተናውን ለማለፍ ስለ ኣውስትራሊያ እሴቶች የሚያተኩሩት ኣምስት ጥያቄዎችን በትክክል ከመለሱ በኋላ የፈተናውን 75 በመቶ መመለስ ይጠበቅብዎታል።

የዜግነት ፈተና የሚካሄደው በሁሉም የኣውስትራሊያ ኣካባቢዎች በሚገኙት የኣገር ውስጥ ጉዳይ መምሪያ ቢሮዎች ነው። በተጨማሪም ፈተናዎቹ በገጠሩ የኣውስትራሊያ ኣካባቢዎችና በኣንዳንድ የባህር ማዶ ሚስዮኖች ይሰጣሉ።

## የኣውስትራሊያ ዜግነት ፈተና ለመፈተን መዘጋጀት

የኣውስትራሊያ ዜግነት ፈተና ለመፈተን ለመዘጋጀት *የኣውስትራሊያ ዜግነት የሚለውን መፅሃፍ ማንበብ ያስፈልግዎታል። የጋራ ማስተሳሰሪያችን*

ይህ መፅሃፍ ፈተና የሚወጣባቸውና የማይወጣባቸው ክፍሎች ኣሉት።

### ፈተና የሚወጣባቸው ክፍሎች

የዜግነት ፈተናውን ለማለፍ የሚያስፈልግዎት መረጃዎች ከክፍል ኣንድ እስከ ኣራት ያሉት የመጽሃፉ ክፍሎች ናቸው።

- ክፍል 1— ኣውስትራሊያና ህዝቧ
- ክፍል 2— የኣውስትራሊያ ዲሞክራሲያዊ እምነቶች፣ መብቶችና ነፃነቶች
- ክፍል 3— መንግስትና ህግ በኣውስትራሊያ
- ክፍል 4— የኣውስትራሊያ እሴቶች

ማወቅና መረዳት ያለብዎት መረጃዎችን ፈተና ከሚወጣባቸው ክፍሎች ውስጥ ኣጥንተው የዜግነት ፈተናውን መመለስ ይችላሉ።

### ለፈተና የማይቀርቡ ጥያቄዎች

ፈተና የማይወጣባቸው ክፍሎች ስለ ኣውስትራሊያ ታሪክና ባህል ጠቃሚ መረጃዎች እንዲረዱ ይረዳዎታል። ለዚህ መረጃ ኣይፈተኑም

- ክፍል 5— የዛሬይቱ ኣውስትራሊያ
- ክፍል 6— የኣውስትራሊያችን ታሪክ

### የመልመጃ ጥያቄዎች

ፈተና ከሚወጣባቸው ክፍሎች መጨረሻ የዜግነት ፈተናውን ለማለፍ ሊረዱ የሚችሉ 20 የመልመጃ ጥያቄዎች ያገኛሉ።

### የቃላት መፍቻ

የቃላት መፍቻ (ቁልፍ የሆኑ ቃላትና ትርጉማቸው) የያዘ ጥያቄ ከሚወጣባቸውና ከማይወጣባቸው ክፍሎች መጨረሻ ላይ ኣለ።

### ተጨማሪ መረጃ

ከመረጃ ምንጩ መፅሃፍ ጀርባ ላይ ተጨማሪ መረጃ ከየት ማግኘት እንደሚችሉ ምክር ያገኛሉ።

### በዜግነት ፈተናው ላይ ሊያገኙ ስለሚችሉት እርዳታ

የኣውስትራሊያ ዜግነት ፈተና ላይ የሚቀመጡ ኣብዛኞቹ ተፈታኞች ኣለ ምንም እርዳታ ለፈተናው የሚበቃ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ ይኖራቸዋል ብለን እንገምታለን። ከጽሁፍ ወደ ንግግር የሚቀይር ቴክኖሎጂ፤ ማለትም ጥያቄውም ሆነ የመልሱ ምርጫ በማዳመጥ የሚመልሱበት ኣማራጭም ኣለ።

### ከኣውስትራሊያ ዜግነት ፈተና በኋላ

ፈተናውን ካለፉ በኋላ ማመልከቻዎ ወደ ፍፃሜው እንዲደርስ እናስኬድልዎታለን። ማመልከቻዎ ተቀባይነት ኣግኝቶ ከፀደቀልዎ በኋላ የዜግነት ስነስርዓቱ ላይ መገኘት ኣለብዎት። በስነስርዓቱ ላይ ለመገኘት የሚያስችል የጥሪ ወረቀት ይላክልዎታል። በኣጠቃላይ ስነስርዓቱ ማመልከቻዎ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ይካሄዳል።

## የኣውስትራሊያ ዜግነት ቃለ መሃላ

ሁላችን የኣውስትራሊያ ዜጎች፤ ዜግነቱን ኣውስትራሊያ በመወለድ ኣገኘነው ወይም በምርጫችን ኣገኘነው መረዳት ያለብን ኣንድ ኣስፈላጊ ነገር ኃላፊነታችንና መብታችን እንዲሁም ዜግነት ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ ነው። ይህ ለሃገራችን ቀጣይ ስኬት በጣም ወሳኝ ነገር ነው።

ለኣውስትራሊያ የዜግነት ስነስርዓት በሚገኙበት ጊዜ የኣውስትራሊያ የዜግነት ቃለ መሃላ ያደርጋሉ።

ይህንን ቃለ መሃላ በሚያደርጉበት ወቅት ለኣውስትራልያ ያልዎት ቁርጠኝነት በኣደባባይ የሚያሳውቁበትና የዜግነት ግዴታዎንና መብትዎን የሚቀበሉበት ነው።

የሚያደርጉት ቃለ መሃላ የሚከተለው ነው።

***ከዚህ ቀን በኋላ፣ ከእግዚኣብሄር*በታች ****

***ለኣውስትራሊያና ለህዝቧ፣***

***ለምጋራው የዲሞክራሲያዊ እምነት***

***ለማከብረው መብትና ነፃነት እንዲሁም***

***ለምታዘዘውና ለምጠብቀው ህግ ለመታመን ቃል እገባለሁ***

*ከእግዚኣብሄር በታች የሚለውን ሃረግ መምረጥ ኣለመምረጥ የግለሰቡ መብት ነው።

ይህን መጽሃፍ ባነበቡ ቁጥር ስለ ቃለመሃላውና ከበስተጀርባው ስላለው ትርጉምና እርስዎ በህብረተሰቡ ውስጥ ሊኖርዎት ስለሚችል ሚና እንዴት ማጎልበት እንደሚችሉ ይረዳሉ።



# የኣውስትራሊያ የዜግነት ስነ ስርዓት

የኣውስትራሊያ የዜግነት ስነስርዓት እንደየሁኔታው ጥቂት ወይም በጣም ብዙ በመቶዎች ወይም በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የሚሳተፉበት ሊሆን ይችላል። ኣዳዲስ ዜጎች የሚኖራቸው ጥልቅ ስሜትና ኩራት እንዲሁም ባለስልጣኖች የሚኖረው የደስታ ስሜት የስነስርዓቱ ድባብ ኣስደሳች በዓል ያደርገዋል።

የዜግነት ክብረ በዓል ሲጀመር የኣገሪቱ ባህላዊ ባለቤት ከሆኑት የቀደምት ኣቦርጅኖችና በቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች /Aboriginal and Torres Strait Islander peoples ተወካይ የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀባበል ይደረጋል። ይህ የሃገሪቱ የእንኳን ደህና መጣችሁ ፕሮቶኮል በሃገሪቱ ባህላዊ ባለቤቶች ዘንድ ለሺ ዘመናት ያህል ተግባራዊ ሲሆን የቆየ ልምድ ነው። ከሌሎች የአካባቢዎ የማህበረሰብ ወይም መንግሥታዊ ተወካይ መሪዎችም የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክትና ማበረታቻም ይተላለፋሉ።

የአውስትራሊያ የዜግነት ቃል ኪዳን ጮክ ብለው በማንበብ ወይም ከሌሎች አዲስ የአውስትራሊያ ዜግነት ከመረጡ ዜጎች ጋር በመሆን ቃል ይገባሉ። ይህ በጣም አስፈላጊ የሆነው የክብረ በዓሉ ክፍል ነው። ይሄንን ለአውስትራሊያ ያልዎትን ቁርጠኝነት ቃል ኪዳን ካልገቡ በስተቀር የኣውስትራሊያ ዜግነት ኣያገኙም።

ቃለ መሃላውን በሚፈፅሙበት ጊዜ የሚይዙትን መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው መምጣት ይችላሉ ፤ ነገር ግን ይሄን ማድረግ ግዴታ አይደለም።

ከማህበረሰብዎ መሪዎች ወይም ከመንግሥት ተወካዮች ስለ ዜግነት ትርጉምና ምንነት አጭር ንግግር ይደረጋል። የአውስትራሊያ ዜግነት የምስክር ወረቀትዎን ከተቀበሉ በኋላ ከማህበረሰቡ ትንሽ ስጦታ ሊሰጥዎት ይችላል። ማንኛውም ሰው 'ኣውስትራሊያ ሚዛናዊ ሆነሽ እደጊ/Advance Australia Fair' የሚባለውን ብሄራዊ መዝሙር ይዘምራል ስነ ስርዓቱ ካለቀ በኋላ ከሌሎች የአውስትራሊያ ወገኖችዎ ጋር ተገናኝተው በዓሉን የማክበር እድል ይኖርዎታል።

የአውስትራሊያ ዜጋ በመሆንዎ የተሳካ ዕድል እንዲሆንልዎት እየተመኘን በአውስትራሊያ ሰላማዊና ፍሬያማ ሕይወት እንዲያጋጥምዎ ምኞታችን ነው።

## ለተጨማሪ መረጃ

የኣውስትራልያ ዜግነት የሚለውን ድረ ገፅ www.citizenship.gov.au ላይ ይጎብኙን።





# ለፈተና የሚቀርበው ክፍል መጀመሪያ



# ክፍል ኣንድ

# ኣውስትራሊያና ህዝቧ

# ኣውስትራሊያና ህዝቧ

በዜግነት ክብረ በዓል ላይ ለኣውስትራሊያና ለህዝቧ የሚኖርዎት የታማኝነት ቃል ኪዳን ይገባሉ። ስለ ኣውስትራሊያ ማህበረሰብና ህዝቡ እንዲሁም የቀደምት ነዋሪዎች ውርስ መረዳት ያስፈልግዎታል። ስለ ኣውስትራሊያ ታሪክና እንደዚህ ወደ ተረጋጋና የተሳካ ህብረ ባህላዊ ሃገር እንዴት እንደደረስን መረዳት ጠቃሚ ነው።

በዚህ ክፍል ታሪካችንን ለመገንባት ስለተከናወኑ ፍፃሜዎች ያነባሉ። ስለ መንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደሮች እንዲሁም እንደ ኣውስትራሊያውያን የምንታወቅባቸው ባህሎቻችንና ምልክቶቻችን መረጃ ያገኛሉ።

## ስለ ኣቦርጅኖችና የቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች /Aboriginal and Torres Strait Islander peoples

ኣቦርጅኖችና በቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች በዓለም በጣም ጥንታዊና እስካሁን ቀጣይነት ያለው ባህልና ልምድ ያላቸው ቀደምት የኣውስትራሊያ ነዋሪዎች ናቸው።

በታሪክ የኣቦሪጂን ህዝብ በኣውስትራሊያ ዋናው ምድርና ታዝማንያ ውስጥ ሲኖሩ ቆይተዋል። የመሬት ውስጥ የቅርስ ጥናት/ኣርኪዮሎጂ እንደሚያመለክተው የኣቦሪጂን ህዝቦች ከ65,000 እስከ 40,000 ዓመታት በፊት ወደ ኣውስትራሊያ እንደመጡ የሚያመለክት ሲሆን፤ እነሱ ግን የዚች ምድር የፍጥረት ታሪክ ማእከል እንደሆኑና የመፈጠራቸው ታሪክ የተጀመረውም ይህች ምድር ስትፈጠር ጀምሮ እንደሆነ ያምናሉ። ቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች በኩንስላንድ ሰሜናዊ ጫፍና በፓፓዋ ኒው ጊኒ መሃከል ይኖራሉ።

ኣቦሪጂኖችና ቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች እድሜ ጠገብ እምነትና ባህል ያላቸው ሲሆን እስከ ኣሁን ድረስም ይመሩበታል ከምድሪቱ ጋር በጣም የጠበቀ ቁርኝት ያላቸውና ታሪካቸው፣ ስነ-ጥበባቸውና ጭፈራቸው የተያያዘ ነው። ሃገር-በቀል ባህሎች በጣም የተለያዩና ለኣውስትራሊያ በጣም ጠቃሚ የማንነት ምንጭ ናቸው።

ስለ ኣቦሪጂኖችና ቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ *በክፍል 5, የዛሬይቱ ኣውስትራሊያ* እና *ክፍል 6, የኣውስትራሊያ ታሪካችን* ማግኘት ይችላሉ

## የመጀመሪያዎቹ የኣውሮፓውያን ሰፋሪዎች

የኣውሮፓውያን ሰፈራ የተጀመረው ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጀለኞችን ይዘው በመጡት 11 መርከቦች ኣማካኝነት ነው። እነዚህ መርከቦች /First Fleet/ በመባል የሚታወቁ ሲሆን እ ኤ ኣ ጥር 26 ቀን 1788 ከብሪታንያ የመጡ ናቸው።

በወቅቱ የብሪታንያ ህግ ጥብቅና ኣስቸጋሪ ስለነበረና ከነበሩት የእስረኞች ቁጥር ኣንፃር እስር ቤቶቹ ከያዙት በላይ መያዝ ኣልቻሉም ነበር። ይሄንን ችግር ለማቃለል የብሪታንያ መንግስት እስረኞቹን በሌላው የዓለም ክፍል ወደ ነበረው የኒው ሳውዝ ዌልስ ቅኝ ግዛት መጓጓዝ እንዳለባቸው በመወሰኑ ነው።

የኒው ሳውዝ ዌልስ ቅኝ ግዛት የመጀመሪያው ገዢ ካፒቴን ኣርተር ፊሊፕ ይባላሉ። ብዙ ወንጀለኞችና ነፃ ሰፋሪዎች እየበዙ ሲመጡ ቅኝ ግዛቱ እየጠነከረ፣ እያደገና እየለማ መጣ። ተጨማሪ ቅኝ ግዛቶችም በሌላው የኣውስትራልያ ክፍል እየተቋቋሙ መጡ።

የመጀመሪያዎቹ ነፃ ሰፋሪዎች የመጡት ከታላቋ ብሪታንያና ከኣየርላንድ ነበሩ። የብሪታንያና የኣየርላንድ ቅርስ በኣውስትራሊያ የቅርብ ጊዜ ታሪክ፣ ባህልና ፖለቲካ ከፍተኛ ተፅእኖ ኣሳደረ።

በ1851 ዓ/ም 'የወርቅ ጥድፊያ / gold rush' የሚባል በኒው ሳውዝ ዌልስና ቪክቶሪያ ከፍተኛ የወርቅ መኣድን የማውጣት ስራ ተጀመረ ከብዙ የዓለም ሃገራት የተሻለ ዕድል ፍለጋ ወደነዚህ ቅኝ ግዛቶች መጡ። ከኣውሮፓ ቀጥሎ ከሌላው ዓለም በብዛት የመጡ ህዝቦች ቻይናውያን ነበሩ። በ 10 ዓመት ውስጥ የኣውስትራሊያ የህዝብ ብዛት ከእጥፍ በላይ ኣደገ።



# ሃገረ ኣውስትራሊያ

በ1901 ዓ/ም ተለያይተው ይኖሩ የነበሩት ግዛቶች በፌደራሲዮን ተባብረው የኣውስትራልያ የጋራ ብልፅግና /the Commonwealth of Australia. በመባል ተጠሩ፡፡ ብሔራዊ ምክር ቤት፣ መንግስት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጨምሮ የኛ ብሔራዊ ዲሞክራቲክ ተቋማት በአውስትራሊያ ሕገመንግስት መሰረት የተቋቋሙት በዚህን ጊዜ ነበር። በ1901 የአውስትራሊያ የሕዝብ ቁጥር አራት ሚሊዮን ገደማ ነበር። ይህ ቁጥር ኣቦሪጂኖችና ቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦችን በ1967 ዓም ሪፈረንደም ተካሂዶ የኣውስትራሊያ የህዝብ ብዛት ውስጥ እስከተካተቱበት ጊዜ ድረስ እነሱን ኣያጠቃልልም ነበር፡፡

እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ኣጋማሽ ድረስ የፍልሰት መጠኑ ከፍና ዝቅ ሲል ቆይቷል፡፡ ብሪታንያውያን ፈላሾች በተለይ እዚህ መጥተው እንዲሰፍሩ ለማበረታታት ታቅደው በትጋት ሲሰራባቸው የነበሩ መርሃ ግብሮች ነበሩ፡፡ ብዙ ሰዎችም መጥተዋል፡፡

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ከብሪታንያውያን ውጭ የሆነ የህዝብ ማዕበል መምጣት ጀመረ፡፡ በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ኣውሮፓውያን ትውልድ ኣገራቸውን መልቀቅ በነበረባቸው ዘመን ማለት ነው፡፡ በጣም ብዙ ኣውሮፓውያን በኣውስትራሊያ ኣዲስ ህይወት ለመገንባት መጡ፡፡

በቅርብ ዓመታት ደግሞ የፍልሰትና የጥገኝነት ጠያቂዎች መርሃግብራችን ኣማካኝነት ከመላው ዓለም ብዙ ሰዎች ወደ ኣውስትራሊያ እንዲመጡ ተደረገ፡፡ ሰዎች ከቤተሰቦቻቸው ለመቀላቀል፣ ኣዲስ ህይወት ለመመስረት፣ ወይም ከድህነት፣ ከጦርነት ወይም ከመሳደድ ለማምለጥ መጥተዋል፡፡


የኣውስትራሊያውያን ብዝሃነት ባለፉት ሁለት መቶ ክፍለ ዘመን በጣም ጨምሯል፡፡ ይህ ብዝሃነት ያለውና የበለፀገ ማህበረሰብ ኣውስትራሊያ ከዓለም ሃገራት ያላትን ግንኙነት ያጠናክረዋል፡፡ የኣውስትራልያ ህዝቦች ብዝሃነት እያከበርን፤ የተባበረችና ጠንካራ ሃገር የመገንባት ዓላማ ኣለን፡፡

የኣውስትራሊያ ብሄራዊ ቋንቋ እንግሊዝኛ ነው፡፡ የማንነታችን ኣንዱ ክፍል ነው፡፡ የኣውስትራሊያን እሴቶች እየጠበቁ፤ መጤዎች በኣውስትራልያ ማህበረሰብ ውስጥ ለመሳተፍ እንዲረዳቸው እንግሊዝኛ መማርና መጠቀም ኣለባቸው፡፡ በኣውስትራሊያ ለመማር ለመስራትም ሆነ የተሻለ ኑሮ ለመኖር በእንግሊዝኛ መግባባት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

ለመኖር በእንግሊዝኛ መግባባት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ከ100 በላይ የሚሆኑ የተለያዩ የአቦሪጂናል እና ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ህዝቦች ቋንቋዎችን ጨምሮ ሌሎች ቋንቋችም በክብር ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡


# የኣውስትራሊያ መንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደሮች /states and territories

የኣውስትራሊያ የጋራ ብልፅግና /Commonwealth of Australia/ የመንግስታትና ክልሎች ፌደሬሽን ነው። ስድስት መንግስታትና /states/ ሁለት የምድር /mainland/ ክልሎች /territories/ ኣሉ። ካንቤራ የኣውስትራሊያ ዋና ከተማ ስትሆን እያንዳንዳቸው መንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደሮች የየራሳቸው ዋና ከተማ ኣላቸው።





| መንግስታዊ ኣስተዳደር / State | ዋና ከተማ |
|---|---|
| ኒው ሳውዝ ዌልስ /New South Wales (NSW) | ሲድኒ / Sydney |
| ቪክቶሪያ / Victoria (Vic.) | ሜልበርን / Melbourne |
| ኲንስላንድ / Queensland (Qld) | ብሪዝቤን / Brisbane |
| ዌስተርን ኣውስትራሊያ / Western Australia (WA) | ፐርዝ / Perth |
| ደቡብ ኣውስትራሊያ / South Australia (SA) | ኣደላይድ / Adelaide |
| ታዝማኒያ / Tasmania (Tas.) | ሆባርት / Hobart |
| **ክልላዊ ኣስተዳደሮች / Territories** | **ዋና ከተማ** |
| ኣውስትራሊያን ካፒታል ተሪተሪ / Australian Capital Territory (ACT) | ካንቤራ / Canberra |
| ኖርዘርን ተሪተሪ / Northern Territory (NT) | ዳርዊን / Darwin |

## መንግስታዊ ኣስተዳደሮች



**ኒው ሳውዝ ዌልስ** የመጀመሪያኣ የብሪታንያ የተመሰረተች ቅኝ ግዛት ናት ሲድኒ የኒው ሳውዝ ዌልስ ዋና ከተማና የሃገሪቱ ትልቋ ከተማ ናት የሲድኒ ሃርበር ድልድይና/The Sydney Harbour Bridge/ የኦፔራ ቤት /Opera House/ የሃገሪቱ ድንቅ መለያዎች ናቸው።.



**በቆዳ ስፋቷ ቪክቶሪያ** በዋናው ምድር ትንሿ መንግስራዊ ኣስተዳደር ናት የቪክቶሪያ ዋና ከተማ ሜልበርን ናት ብዙ ረቂቅ የሆኑ የቪክቶሪያ ህንፃዎች የተገነቡት በ 1850ዎቹ በነበረው /gold rush/ በሚባል ጊዜ ከተፈጠረው ሃብት ነው። የቪክቶሪያ መለያዎች የሜልበርን የክሪኬት ሜዳ /Melbourne Cricket Ground/ ኣስራ ሁለቱ ሃዋርያት /the 12 Apostles/፣ እና ንጉሳዊ የኤግዚቪሽን ህንፃ /the Royal Exhibition Building/ ናቸው።




**ኩንስላንድ** በቆዳ ስፋቷ ሁለተኛዋ ትልቋ መንግስታዊ ኣስተዳደር ና። የኩንስላንድ ዋና ከተማ ብሪዝቤን ናት። የቶረስ ባህረ ሰላጤ ደሴቶች ከዚህ መንግስታዊ ኣስተዳደር ሰሜናዊ ክፍል ሲሆን በዓለም ላይ በጣም ዝነኛ የሆነው /Great Barrier Reef/ በምስራቃዊው የባህር ዳርቻ ይገኛል። ኩንስላንድ የምድር ወገብ ዝናባማ ደኖች፣ ነፋሻ የባህር ዳርቻ ቦታዎችና ብዙ ጊዜ ደረቅ የመሃል መሬት ኣላት።



**ምዕራብ ኣውስትራሊያ በቆዳ ስፋቷ** ትልቋ መንግስታዊ ኣስተዳደር ናት። ፐርዝ የምዕራብ ኣውስትራሊያ ዋና ከተማ ናት። ምስራቃማው ክፍል ኣብዛኛው ምድረ በዳ ሲሆን ደቡባዊ ምዕራቡ ግን ሃብታም የእርሻና የወይን ተክል ማምረቻ ቦታ ነው። መንግስታዊ ኣስተዳደሩ ብዙ የማእድን ማውጫ ፕሮጀክቶች ኣሉት። የምዕራብ ኣውስትራሊያ ታዋቂ ቦታዎች የኒንግሉ የባህር ዳርቻ፣ ማርጋሬት ወንዝና የኪምበርሊ ኣካባቢ ናቸው።




**ደቡብ ኣውስትራሊያ** ወጣ ገባ የሆነ የባህር ዳርቻና በጣም ታዋቂ የወይን ቦታዎች ያላት መንግስታዊ ኣስተዳደር ናት። ዋና ከተማዋ ኣደላይድ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ብዙ ረቂቅ የቅኝ ግዛት ጊዜ ስነ ህንፃዎች ኣሏት። የደቡብ ኣውስትራሊያ ታዋቂ ምልክቶች የባሮሳ ሸለቆና የፍሊንደርስ የግጦሽ ቦታ ይገኙበታል።




**ታዝማኒያ** በጣም ትንሿ መንግስታዊ ኣስተዳደር ስትሆን ከዋናው ምድር ባስ በተባለ የባህር ወሽመጥ ተለይታለች። የታዝማኒያ ዋና ከተማ ሆባርት ትባላለች። ኣብዛኛው መሬቷ ብዙ ያልተነካ በጫካ የተሸፈነ መልክኣ ምድር ኣላት። የታዝማኒያ ታዋቂ ቦታዎች የክሬድል ተራራ፣ የኣርተር ወደብና ቤይ ኦፍ ፋየርስ ናቸው።

## ክልላዊ ኣስተዳደሮች



**ኣውስትራሊያን ካፒታል ተሪተሪ** በሲድኒና በሜልበርን ከተሞች መሃል ትገኛለች። የሃገሪቱ ዋና ከተማ የሆነችው የካንቤራ ከተማ በዚሁ ክልል ትገኛለች። ብዙ ብሄራዊ ተቋማት ካንቤራ ውስጥ ይገኛሉ። ከነዚህም ውስጥ የፓርላሜንት ሃውስና የኣውስትራሊያው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይገኙበታል።



**ሰሜናዊ ክልላዊ ኣስተዳደር** ትሮፒካዊ የኣየር ንብረት በሰሜናዊው ክፍል ደረቅና ቀይ ምድረ-በዳ በደቡቡ ክፍል ይገኛል። ዳርዊን ዋና ከትማዋ ነች። የሰሜናዊ ክልላዊ ኣስተዳደር ታዋቂ ቦታዎች ኡሉሩ፣ ካታ፣ ቱጁታና ኪንግስ ካንዮን ናቸው።



# ባህሎችና ወጎች

## ለሃገራዊ ፕሮቶኮል እውቅና ወደሚሰጥበት ኣገር እንኳን በደህና መጡ

እንኳን ደህና መጡ ማለት የኣካባቢው ጠባቂዎች በሆኑት ኣቦርጂኖችና በቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች እንግዶች ወደ ታሪካዊ ምድራቸው ሲመጡ ሲተገብሩት የኖሩ ባህላዊ ልምዳቸው ነው። ይሄ ተግባር ሲፈፀም የኖረው ማንኛውም እንግዳ ወደ ኣካባቢያቸው መጥቶ በሚጓዝበት ወቅት ምንም ኣደጋ ሳይደርስበት እንዲንቀሳቀስ ዋስትና የሚሰጡበት መንገድ ነው።

ወደዚህ ኣገር እንኳን በደህና መጡ የሚባለው በዘፈን፣ በጭፈራ፣ በማጨስ ስነስርዓት ወይም በባህላዊ ቋንቋ ወይም በእንግሊዝኛ በመናገር ጨምሮ በተለያየ መንገድ ነው።

ወደዚህ ኣገር እንኳን በደህና መጡ የሚባለው ብዙ ጊዜ ማናቸውም ድርጊት መግቢያ ላይ የሚከናወን ተግባር ነው።

የኣገር እውቅና መስጠት ማለት የኣቦርጂኖችና የቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኞች መሬት ላይ ለሚያደርጉት መሰባሰብ እውቅና ለመስጠት፤ ለባህላዊ ጠባቂዎች ክብር መስጠት በተለይም በፊት ለነበሩና ኣሁን ላሉ ትልልቅ ኣዛውንቶች፤ እንዲሁም በስብሰባው ቦታ ለተገኙት ለኣቦርጂኖችና በቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች ተገቢውን ክብር የሚሰጥበት መድረክ ነው።

የሃገር እውቅና መስጠት ብዙ ጊዜ የሚሰጠው እንደ የእንኳን ደህና መጣችሁና የቤት ጥበቃ ኣካል ሆኖ በሚደረግ ስብሰባና ጉዳይ ላይ ነው። ማንም ሰው የኣገር እውቅና ንግግር ማድረግ ይችላል። ይህም የሚደረገው በስብሰባ/ጉዳይ ላይ ሲሆን የሚፈፀመውም ስነ ስርዓቱን በሚመራው ሰው ነው።
ይሄ ስነስርዓት የሚከናወነውም ለኣቦርጂኖችና በቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች ክብር ለመስጠት ነው።



# የኣውስትራሊያ ዓመታዊ ክብረ በዓላት

## የኣውስትራሊያ ቀን

የአውስትራሊያ ቀንን በየአመቱ 26 ጥር /January/ እናከብራለን። የኣውስትራሊያ ቀን በአውስትራሊያ ውስጥ ባሉ እያንዳንዱ መንግስትና ክልል ህዝባዊ በዓል ነው። ይህ በዓል የሚከበረው ጥር 26 ቀን 1788 ዓ.ም ሲሆን ከብሪታንያ የደረሱትን የመጀመሪያ መርከቦች ለማስታወስ ነው።

በኣውስትራሊያ ቀን በዓል በመላው አውስትራሊያ ማህበረሰባት ዘንድ ስለ አውስትራሊያ ታሪክ፣ እንዲሁም ህዝቦቿ ለጋራ ስኬቷ ስላደረጉት ኣስተዋፅኦ የሚንፀባረቅበት ቀን ነው። በኣውስትራልያ ትልቁ ህዝባዊ በዓል ይኸው ነው።

የኣውስትራሊያ ቀን የሚከበረው ይህቺ ኣገር በኣሁኑ ዘመን ለደረሰችበት ምጥቀት፤ ከኣቦርጂኖችና ቶረስ የ ባህር ወሽመጥ ደሴተኞች ለ65000 ዓመታት ያህል ከኖሩበት ጊዜ ጀምሮ ከተለያየ ዓለም መጥተው ኣውስትራሊያን የመኖሪያ ሃገራቸውን በማድረግ ለትውልድ እስከ ኖሩት ሁሉ ላበረከቱት ኣስተዋፅኦ እውቅና ለመስጠትና ለማክበር ነው። ልዩ ዜግነትን ጨምሮ የአውስትራሊያ ቀን በልዩ ልዩ ዝግጅት በመላው አውስትራሊያ ተከብሮ ይውላል።

በኣውስትራሊያ ቀን በዓል ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የዓመቱ ኣውስትራሊያዊ ሽልማት ተሸላሚ በካንቤራ ያሳውቃሉ።

## የአንዛክ ቀን /Anzac Day

በየዓመቱ ሚያዚያ 25 ቀን የአንዛክ ቀን /Anzac/ ቀን ይከበራል። አንዛክ ቀን/Anzac Day ተብሎ የተሰየመው በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ሚያዝያ 25 ቀን 1915 ዓ.ም ቱርኪዬ/Türkiye ውስጥ በሚገኘው ጋሊፖሊ ባረፈው የአውስትራሊያና የኒው ዚላንድ ጦር ሰራዊት ስም ነው።

የኣንዛክ ቀን ለሰላም ማስከበር ተልእኮ ሄደው ላገለገሉና በጦርነቱ ህወታቸውን ላጡ አውስትራውያን በማስታወስ በፅሞና የሚከበርና በዓል ነው። በተጨማሪም በምንሳተፍባቸው ሌሎች ዓውደ ውጊያዎች ሁሉ በጀግንነትና ቆራጥነት ላገለገሉት ወንድና ሴቶች ሁሉ በማክበር የነዚህ ቆራጥነት እናንፀባርቃቸዋለን።

ስለ ሌሎች ብሄራዊ ቀናትና በዓላት ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ በክፍል *5, የዛሬይቱ ኣውስትራሊያ*/Australia today/ በሚለው ላይ ይፈልጉ።

# የአውስትራሊያ ባንዲራዎች

የአውስትራሊያ ብሄራዊ ባንዲራ የሃገሪቷ ብሄራዊ ባንዲራ ነው። ሌሎች እውቅና የተሰጣቸው የሚውለበለቡ ባንዲራዎች ያሉ ሲሆን እነዚህም የአውስትራሊያ አቦርጂናል ባንዲራና የቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኞች ባንዲራ ናቸው።

በተጨማሪም እያንዳንዱ መንግስታዊና ክልላዊ መስተዳድር የየራሱ ባንዲራ ይኖረዋል። እነዚህም በገጽ 11 ላይ ይገኛሉ።

## የአውስትራሊያ ብሄራዊ ባንዲራ

የአውስትራሊያ ብሄራዊ ባንዴራ ሰማያዊ፣ ነጭና ቀይ ነው።

- ‘የህብረት ኣርማ /’Union Jack’/ የሚባለው የእንግሊዝ ባንዲራ በባንዲራው ግራ ላይኛው ጫፍ ኣለ። ይህም የእኛዎቹ የብሪቲሽ ሰፋሪዎችን ታሪክ እንዲሁም በዚህ የተነሳ በውርስ ያገኘናቸው ሕጎች እና ተቋማትን ይወክላል።
- የጋራ ብልፅግናው /Commonwealth/ ኮከብ ከህብረቱ ምልክት /Union Jack/ በታች ኣለ። ይህ ኮከብ ሰባት ጫፎች ኣሉት ይኸውም የሚያመለክተው ስድስቱ ጫፎች መንግስታቱን ሲሆን ኣንዱ ጫፍ ደግሞ ክልሎችን ያመለክታል።
- በቀኝ በኩል ያለው በኮከቦች ስብስብ የተሰራው ደቡባዊ መስቀል /Southern Cross/ በደቡባዊ ሰማይ ላይ ይታያሉ።



## የአውስትራሊያ አቦርጂናል ባንዲራ



የአውስትራሊያ አቦርጂናል ባንዲራ ጥቁር፣ ቀይና ብጫ ነው።

- የላይኛው ግማሽ ጥቁር ነው ይኸውም የኣውስትራሊያን ኣቦሪጅኖችን ይወክላል።
- የታችኛው ግማሽ ቀይ ነው መሬትን የሚወክል ሲሆን ይህም ከክብረ በዓል ጋር የተያያዘ ጠቀሜታ ኣለው።
- የመሃለኛው ብጫ ክብ ፀሃይን ይወክላል።

## የቶረስ ስትሬት አይላንደርስ ባንዲራ

የቶረስ ባህረ ሰላጤ ደሴተኞች ባንዲራ አረንጓዴ፣ ሰማያዊ፣ ጥቁርና ነጭ ነው።

- ኣረንጓዴ ሸንተረር መሬትን ይወክላል።
- መሃል ላይ ያለው ሰማያዊ ሰሌዳ ባህሩን ይወክላል።
- ጥቋቁር መስመሮቹ ደግሞ ባህረ ሰላጤ ደሴተኛ ህዝቦችን ይወክላል።
- በመሃል ላይ ያለችው ነጯ የጨፋሪዎች የፀጉር ኣሰራር ሁሉንም የቶረስ ባህረ ሰላጤ ደሴተኞችን ትወክላለች።
- የነጯ ኮከብ ጫፎች ደግሞ የቶረስ ስትሬት ደሴቶችን ነጩ ቀለም ደግሞ ሰላምን ያመለክታል።



# የኣውስትራሊያ ምልክቶች

## የጋራ ብልፅግና ኣርማ

የጋራ ብልፅግናው ኣርማ የኣውስትራሊያ የጋራ ብልፅግና ህጋዊ ኣርማ ነው። ብሄራዊ ኣንድነታችንን ይወክላል። የኣውስትራሊያ የጋራ ብልፅግና ስልጣንና ንብረት መሆኑን ያመለክታል።

- መሃል ላይ ያለው ጋሻ ስድስቱ መንግስታትና ፌደረሽኑን ይወክላል።
- ካንጋርዋና ኢሙዋ ጋሻውን ከግራና ቀኝ ደግፈውታል። ሁለቱም የኣውስትራሊያ ሃገራዊ እንስሳት ናቸው።
- ወርቃማ የጋራ ብልፅግና ኮከብ ጋሻው ላይ ተቀምጧል።
- ከኋላ ወርቃማ ዋትል የሚባል የኣውስትራሊያ ሃገር በቀል ኣበባ ኣለ።





## የአውስትራሊያ ብሄራዊ አበባ

የኣውስትራሊያ ብሄራዊ ኣበባ ወርቃማ ዋትል ነው። ይህ ኣበባ በኣብዛኛው በደቡባዊ ምስራቅ ኣውስትራሊያ ይበቅላል። ብሩህ ኣረንጓዴ ቅጠሎችና ብዙ ወርቃማ ቢጫ ኣበቦች በፀደይ ወቅት ኣለው። እያንዳንዱ የኣውስትራሊያ የመንግስትና ክልላዊ ኣስተዳደሮች የራሳቸው የኣበባ ኣርማ ኣላቸው።



## የኣውስትራሊያ ብሄራዊ ቀለማት

የአውስትራሊያ ብሄራዊ ቀለማት አረንጓዴና ወርቃማ ሲሆኑ ይኸውም የወርቃማው ዋትል ቀለም ነው። የብሄራዊ ስፖርት ቡድኖቻችን መለያ ልብስ አብዛኛው አረንጓዴና ወርቃማ ቀለሞች ናቸው።





## የኣውስትራልያ ብሄራዊ የከበረ ድንጋይ

የኣውስትራልያ ብሄራዊ የከበረ ድንጋይ ኦፓል/መረግድ ነው። እንደ አቦርጅናል አፈታሪክ አባባል የሰማይ ቀስተ ደመና መሬትን ሲነካ የኦፓል/መረግድን ቀለማት ፈጠረ ይላሉ።



# የኣውስትራሊያ ብሄራዊ መዝሙር

‘ኣውስትራሊያ በፍትህ እደጊ’/‘Advance Australia Fair’ የኣውስትራሊያ ብሄራዊ መዝሙር ነው። የኣውስትራሊያ የዜግነት ስነስርዓት በሚካሄድበት ጊዜ ጨምሮ እንደ ትልልቅ የስፖርት ውድድሮችና የመሳሰሉት ብሄራዊ ትርጉም ባላቸው በዓላት ላይ ይዘመራል።

## ኣውስትራሊያ በፍትህ እደጊ /Advance Australia Fair

*Australians all let us rejoice,*
*For we are one and free;*
*We've golden soil and wealth for toil;*
*Our home is girt by sea;*
*Our land abounds in nature's gifts*
*Of beauty rich and rare;*
*In history's page, let every stage*
*Advance Australia Fair.*
*In joyful strains then let us sing,*
*Advance Australia Fair.*

*Beneath our radiant Southern Cross*
*We'll toil with hearts and hands;*
*To make this Commonwealth of ours*
*Renowned of all the lands;*
*For those who've come across the seas*
*We've boundless plains to share;*
*With courage let us all combine*
*To Advance Australia Fair.*
*In joyful strains then let us sing,*
*Advance Australia Fair.*



# ክፍል ሁለት

## የኣውስትራሊያ ደሞክራሲያዊ እምነት, መብትና ነፃነት

# የኣውስትራሊያ ደሞክራሲያዊ እምነት፣ መብትና ነፃነት

በዜግነት ስነስርዓቱ ላይ የኣውስትራሊያን ዲሞክራሲያዊ እምነቶች በጋራ ለመጠቀምና መብትና ነፃነት ለማክበር ቃል ይገባሉ፡፡ የኣውስትራሊያን ዲሞክራሲያዊ እምነቶችንንና መብትና ነፃነቶችን በሚገባ መረዳት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

ይህ ጥራዝ እነዚህን እምነቶች፣ መብቶችና ነፃነቶችን ይዘረዝራል፡፡ ለተጨማሪ መረጃ *የክፍል 4፤ የኣውስትራሊያ እሴቶች* የሚለውን ይመልከቱ፡፡

## ዲሞክራሲያዊ እምነታችን

### ፓርላሜንታሪያዊ ዲሞክራሲ

የአውስትራሊያ መንግሥታዊ አሠራር የፓርሊያመንታዊ የዲሞክራሲ ስርዓት ነው፡፡ እንደ ኣንድ የስርዓቱ ክፍል የመንግስቱ ስልጣን የሚመነጨው ከኣውስትራሊያ ህዝቦች ሲሆን የአውስትራሊያ ዜጎች እነሱን በፓርላማ ለሚወክሏቸው ሰዎች ድምፃቸውን በመስጠት ነው፡፡ በፓርላማ ያሉት ወኪሎች ስለሚወስኑት ውሳኔ በምርጫ ለህዝቡ ምላሽ መስጠት ይገባቸዋል፡፡

### የህግ የበላይነት

በህግ ፊት ሁሉም ኣውትራሊያውያን እኩል ናቸው፡፡ በህጉ መሠረት ግለሰብ፣ቡድን ወይም የሃይማኖት ህጎች ከህግ በላይ አይደሉም። ማንኛውም ሰው የኣውስትራሊያ መንግስት ባለስልጣናትን ጨምሮ ለአውስትራሊያ ህግ ተገዥ መሆን አለበት፡፡ ይህም የመንግስት፣ የማህበረሰብ፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የንግድ ሰዎችም ሆነ ፖሊስን ያካትታል፡፡

### በሰላም ስለመኖር

ኣውስትራሊያውያን በዚህ ሰላማዊና የተረጋጋ መንግስታዊ ስርዓት የሚኖ በመሆናቸው ኩራት ይሰማቸዋል፡፡ በኣውስትራሊያ ለውጥ መምጣት የሚገባው በውይይት፣ በሰላምና በመተማመን እንዲሁም በዲሞክራሲያዊ ሂደት ነው፡፡ ዓመፅ የሰዎችን ወይም የህግ መለወጫ መንገድ እንዲሆን ኣንቀበለውም፡፡

### የሰዎች የኋላ ታሪካቸው ግምት ውስጥ ሳይገባ ሁሉም ግለሰቦችን በእኩልነት ማክበር

በአውስትራሊያ ዲሞክራቲክ ደንብ መሠረት ማንኛውም ግለሰብ ምንም ይሁን ምንም በአውስትራሊያ ሕግ ፊት እኩል መብት አለው፡፡ ሁሉም ኣውስትራሊያውያን ዘር፣ የመጡበት ኣገር፣ ፆታ፣ የፆታ ምርጫ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ እድሜ፣ የኣካል መጉደል፣ ኣመጣጡ፣ ባህል፣ ፖለቲካ፣ ሃብት፣ ወይም ሃይማኖት ሳይለይ በእኩልነት እንዲከባበበሩ ይጠበቅባቸዋል፡፡



# ነፃነታችን

## የመናገር ነፃነትና ራስን የመግለፅ ነፃነት

የመናገር ነፃነት ዋናው የአውስትራሊያዊያን እሴት እና የእኛ ዲሞክራቲክ ደንብ መሰረት ነው። የመናገር ነፃነት ማለት ሰዎች የሚፈልጉትንና የሚያስቡትን ነገር የመናገር የመፃፍና ከሌሎች ሰዎች ጋር ሃሳብን በነፃነት መወያየት ማለት ነው። ለምሳሌ ሰዎች መንግስትን መንቀፍ ይችላሉ፣ በሰላማዊ መንገድ የመንግስትን ውሳኔ መቃወም ይችላሉ፣ የኣውስትራሊያን ህግ እስካከበሩ ድረስ የህግ ለውጥ እንዲኖር ዘመቻ ማድርግ ይችላሉ።

ራስን የመግለፅ መብት ማለት ሰዎች ኣስተያየታቸውን በስነጥበብ፣ በፊልም፣ በሙዚቃና ባስነፅሁፍ መግለፅ ይችላሉ ማለት ነው። ሰዎች በማንኛውም የፖለቲካ ርእስ ተገናኝተው በግል ወይም በአደባባይ መወያየት ይችላሉ።

የመናገር ወይም ሃሳብ የመግለፅ መብታችን በምንገልፅበት ወቅት የኣውስትራሊያን ህግ በማንኛውም ሰዓት የማክበር ግዴታ ኣለብን። የሌሎችን ሰዎች የመናገርና ራሳቸውን የመግለፅ መብት የግድ ማክበር ይጠበቅብናል።

## የማህበራት ነፃነት

የማህበራት ነፃነት ማለት ማህበራት መድረስ ወደሚፈልጉት የጋራ ግብ ለመድረስ እንዲችሉ የሚያስችላቸውን ማህበር ለመስረትና ለመተባበር ያላቸው ነፃነት ማለት ነው። ለምሳሌ በኣውስትራሊያ ሰዎች ወደሚፈልጉት ህጋዊ ድርጅት፣ የፖለቲካ ፓርቲ፣ የሰራተኛ ማህበር፣ ሃይማኖት፣ ባህላዊ ወይም ማህበራዊ ቡድን ጋር ለመቀላቀል ሙሉ ነፃነት ኣላቸው። ሕዝቦች አባል ላለመሆን (ላለመሳተፍ) መወሰን ይችላሉ፤ አባል (ተሳታፊ) እንዲሆኑም አይገደዱም።

ኣውስትራሊያዊያን የመንግስትን ወይም የድርጅትን ተግባር ለመቃወም ከሌሎች ጋር መሰባሰብ ይችላሉ። በማናቸውም ሰዓት ግን የኣውስትራሊያ ህግ መከበር ኣለበት። ይህም ማለት እንዲህ ዓይነት መሰባሰቦች ሰላማዊ መሆን ኣለባቸው ማንንም ሰው ሆነ ንብረቱን መጉዳት የለባቸውም።

## የሃይማኖት ነፃነት

አውስትራሊያ የኣይሁድ-ክርስቲያን ውርስ አላት።ብዙ አውስትራሊያዊያን ክርስቲያን እንደሆኑ ራሳቸውን ይገልፃሉ፣ ቢሆንም ግን ከሁሉም ትላልቅ እምነቶች የሚመዘዙ ህዝቦች በአውስትራሊያ ይገኛሉ። አውስትራሊያ እንደ ስቅለት፣ ትንሳኤ እና ገና  የመሳሰሉ  ክርስቲያንናዊ የሕዝብ በዓላት ታከብራለች።

መንግስትና ህግ የየትኛው ሃይማኖትና እምነት ተከታዮች ይሁኑ በእኩልነት ይታያሉ። የአውስትራሊያ መንግስት በሕዝብ አስተዳደር የሚመራ ነው። ይህም ማለት ከቤተክርስቲያን እና ከሌሎች ቤተ እምነቶች ተለይቶ ራሱን ችሎ ይሰራል ማለት ነው። ኣውስትራሊያ ብሄራዊ ሃይማኖት የላትም። በኣውስትራሊያ ያሉት ህዝቦች የመረጡትን ሃይማኖት የመከተል መብት ኣላቸው። ሃይማኖት የለሽ ሆነው መኖር ከመረጡም ይችላሉ።

በማናቸውም ሰዓት የሃይማኖት ስነ ስርዓት ሲያከብሩም ሲሆን የሃገሪቱን ህግ የግድ ማክበር ይጠበቅባቸዋል። በአውስትራሊያ እና በቤተ-እምነት መካከል የሕግ ተቃርኖ ሲያጋጥም የአውስትራሊያው ሕግ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

# እኩልነታችን

በኣውስትራሊያ ማንኛውም ሰው በፆታው፣ በዘሩ፣ በኣካለ ጎደሎነቱ ወይም በእድሜው ምንም ዓይነት ኣድልዎ እንዳይደርስበት የሚከላከሉ በጣም በርካታ ህጎች ኣሉ።

## የፅኦታ እኩልነት።

በኣውስትራሊያ ወንድና ሴት እኩል መብት ኣላቸው። በፆታው ምክንያት ማንኛውንም ሰው ማዳላት ህገ ወጥነት ነው።

## የተጠቃሚነት እኩልነትና ፍትሃዊነት/‘fair go’

ኣውስትራሊያውያን በህብረተሰቡ ዘንድ ለእኩል ተጠቃሚነት ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣሉ። ፍትሃዊነት የሚባለውም ይሄ ነው። ይህም ማለት ኣንድ ሰው የተሳካ ህይወት እንዲኖረው የሚገባው በችሎታው፣ በስራውና በጥረቱ እንጂ በሃብቱና በኣመጣጡ ምክንያት መሆን የለበትም ማለት ነው። ይህም ማለት በኣውስትራሊያ ማህበረሰብ ውስጥ መደበኛ የሆነ የመደብ ልዩነት እንዳይኖር ማስትና ለመስጠት ነው።

# የኣውስትራሊያ ዜጎች መብትና ግዴታ

ኣውስትራሊያዊ በምትሆንበት ሰዓት ተጨማሪ መብትና ግዴታ ይኖርብዎታል።

## ግዴታዎ- እርሰዎ ለኣውስትራሊያ የሚሰጧት ሲሆን

እንደ ኣውስትራሊያ ዜጋ የሚከተሉትን ነገሮች የግድ ማድረግ ይጠበቅብዎታል፤

- የኣውስትራሊያ ህግ ማክበር
- በፌደራል፣ በመንግስትና ክልል ምርጫዎችና ሪፈረንደም መሳተፍ
- ኣስፈላጊ ሲሆን ኣውስትራሊያን መከላከል
- ጥሪ ከተደረገልዎት በሸንጎ ማገልገል

## ልዩ መብትና ጥቅም - ኣውስትራሊያ ለእርሰዎ የምትሰጠው

እንደ ኣውስትራሊያ ዜጋ የሚከተሉትን ያገኛሉ፤

- በፌደራል፣ በመንግስትና ክልል ምርጫዎችና ሪፈረንደም መሳተፍ
- ውጭ ኣገር የተወለዱ ልጆች በወላጆቻቸው ምክንያት ኣውስትራሊያውያን እንዲሆኑ የማመልከት
- በኣውስትራሊያ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ተቀጥሮ ለመስራት የማመልከት
- ለፓርላማ ምርጫ መወዳደር
- የኣውስትራሊያ ፓስፖርት ለማግኘትና ወደ ኣውስትራሊያ በነፃነት ወጥቶ ለመግባት
- በውጭ ሃገር በሚቆዩበት ሰዓት የቆንስላ ኣገልግሎት ለማግኘት የመጠየቅ




# ግዴታዎች

## የኣውስትራሊያን ህግ ማክበር

በመንግስት ያሉት ወኪሎቻችን ስርዓት እንዲከበር፣ የማህበረሰባችን ነፃነትና ደህንነት እንዲከበርንና መብታችን እንዲከበር ህግ ያወጣሉ። ሁሉም የኣውስትራሊያ ዜጎችና ሌሎች በኣውስትራሊያ ያሉ ሰዎች የኣውስትራሊያን ህግ የማክበር ግዴታ ኣለባቸው።

ስለ ኣንዳንድ ጠቃሚ የኣውስትራሊያ ህጎች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የሚከተሉትን ያንብቡ *ክፍል 3፤ መንግስትና ህግ በኣውስትራሊያ*።

## በፌደራል፣ በመንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደሮች ድምፅ የመስጠት

ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ ለሆኑ ሁሉም የኣውስትራሊያ ዜጎች ድምፅ መስጠት ግዴታ፣ መብትና ልዩ ጥቅም ነው።

ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ ለሆኑ ሁሉም የኣውስትራሊያ ዜጎች ለፌደራል ለመንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደሮች እንዲሁም የኣውስትራሊያን ህገ መንግስት ለመቀየር የሚደረግ ሪፈረንደም ድምፅ መስጠት ግዴታ ነው። ይሄንን በማድረግ የኣውስትራሊያ ዜጎች ኣውስትራሊያ በምትተዳደርበትና የወደፊት ዕድሏ የሚወሰንበት ጉዳይ ላይ ወሳኝነት ኣላቸው ማለት ነው።

በፌደራል፣ በመንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደሮች ድምፅ መስጠት ግዴታ ነው። በኣንዳንድ መንግስታዊ ኣስተዳደሮች የኣካባቢ ምርጫ ላይ መሳተፍ ግዴታ ኣይደለም።

ስለ ኣውስትራሊያ ህገመንግስት ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ *P ክፍል 3፤ መንግስትና ህግ በኣውስትራሊያ* ላይ ያንብቡ።

## ኣስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኣውስትራሊያን ይከላከላሉ

በኣውስትራሊያ የመከላከያ ሃይል መሳተፍ በፈቃደኝነት ሲሆን፤ ኣስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኣውስትራሊያን የመከላከል ግዴታም ኣለ። ኣውስትራሊያውያን እጅ ለእጅ ተያይዘው ኣገራቸውን መከላከላቸው በጣም ወሳኝ ሲሆን እንደ ኣስፈላጊነቱም እንደ ባህል መወሰድ ያለበት ጉዳይ ነው።

## ኣገልግሎቱን ለመስጠት ከተጠሩ የሸንጎ ኣባል ሆነው ያገለግላሉ።

የሸንጎ ኣገልግሎት እንዲሰጡ ከተጠየቁ፤ ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ የኣውስትራሊያ ዜጎች የመስጠት ግዴታ ኣለባቸው። ሸንጎ ማለት ተራ የኣውስትራሊያ ወንድና ሴት ዜጎች ሰዎች የሚያቀርቡትን የህግ ጉዳይ በመስማት ጥፋተኛ መሆን ኣለመሆናቸውን የሚወስኑበት መድረክ ነው።

በመራጭነት የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው በሸንጎ ለማገልገል ሊጠራ ይችላል። የሸንጎ ኣገልግሎት የፍትህ ስርዓቱ ግልፅና ፍትሃዊ እንዲሆን የሚረዳ ኣሰራር ነው።

## ልዩ መብትና ተጠቃሚነት

### በኣውስትራሊያ የመንግስት መስሪያ ቤትና በመከላከያ ስራዊት ተቀጥሮ ለመስራት ማመልከት

የአውስትራሊያ ዜግነት ማግኘት በአውስትራሊያ የሕዝባዊ አገልግሎት ሥራ ለማመልከት እና ለአውስትራሊያ መንግስት ለመስራት ይረዳል ለምሳሌ ለአውስትራሊያ አገልግሎት ለመስጠት ወይም አውስትራሊያ ግብር ሰበሰሳቢ መስሪያቤት ለመስራት እንደማለት ነው።

የኣውስትራሊያ ዜጎች በጦር ሃይል፣ (በእግረኛ፣ በባህር ሃይልና በኣየር ሃይል) ኣባልነት ለመስራት ማመልከት ይችላሉ።

### የፓርላማ እጩ ተመራጭ ስለ መሆን

እድሜው ከ18 ዓመትና ከዛ በላይ የሆነ ኣውስትራሊያ ዜግነት ያለው ሰው ለፌደራል፣ ለመንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደር የፓርላማ እጩ ሆኖ መቅረብ ይችላል። የኣውስትራሊያ የፓርላማ ኣባል ሆኖ ማገልገል ታላቅ ክብርና ሃላፊነት ነው።

### የኣውስትራሊያ ፓስፖርት ለማግኘት ማመልከትና ወደ ኣውስትራሊያ በነፃነት መግባትና መውጣት ያስችላል

የኣውስትራሊያ ዜጋ በሚሆኑበት ወቅት በኣውስትራሊያ በነፃነት የመኖር መብት ኣለዎት። የኣውስትራሊያን ፓስፖርት ለማግኘት የማመልከት ልዩ ጥቅም ያስገኛል። የኣውስትራሊያ ዜጋ ሆነው ወደ ኣውስትራሊያ ሲመለሱ ኣለ ምንም ቪዛ ወደ ኣውስትራሊያ የመመለስ መብት ኣልዎት።

### ውጭ ሃገር በሚቆዩበት ጊዜ የኣውስትራሊያ የቆንስላ ኣገልግሎት የመጠየቅ መብት ያገኛሉ

ኣውስትራሊያ በብዙ ሃገራት ኤምባሲ፣ ከፍተኛ ኮሚሽን ወይም የቆንስላ ፅ/ቤት ኣላት። ውጭ ሃገር በሚቆዩበት ጊዜ እርዳታ ከፈለጉ ለኣውስትራሊያ መንግስት ባለስልጣናት መጠየቅ ይችላሉ። ይህም ኣስችኳይ የሆኑ እንደ ህዝባዊ ንቅናቄ፣ ወይም የተፈጥሮ ኣደጋን ያካትታል።

በተጨማሪም በውጭ ኣገር ሆነው እንደ ፓስፖርት፣ ምክርና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሁኔታዎችና ኣደጋዎች ወይም ከፍተኛ ህመም ወይም ሞት የመሳሰሉት ኣስቸኳይ ነገሮች ሲያጋጥሙ የኣውስትራሊያ ባለስልጣናት ሊያግዎት ይችላሉ።

በሌላ ሃገር በሚቆዩበት ጊዜ የሃገሪቱን ህግ ማክበር ግዴታዎ ነው።

### ባህር ማዶ የተወለደውን ልጅ ካልዎት በወላጅነትዎ ለኣውስትራሊያ ዜግነት ሊጠይቁለት ይችላሉ

የኣውስትራሊያ ዜጎች ውጭ ሃገር ለተወለዱት ልጆቻቸው ኣውስትራሊያዊ ዜግነት እንዲያገኙ ሊያመለክቱላቸው ይችላሉ።

# በኣውስትራሊያ ማህበረሰብ ውስጥ ስለመሳተፍ

ኣውስትራሊያ ሁሉም ዜጎች በማህበራዊ ህይወት በንቃት እንዲሳተፉ ታበረታታለች። ንቁ ዜጎች ግዴታቸውንና መብታቸው እየተጠቀሙ የኣገራቸውን የወደፊት እጣ ፈንታ ይቀርፃሉ። ለምሳሌ የመኖሪያ ሰፈርና የኣካባቢው ህዝባዊ ድርጅቶች ጋር ኣባል መሆን ይችላሉ፣ ማህበራዊና ህዝባዊ በሆኑ ተግባራት የመሳተፍ፣ ባህላዊና ስነጥበባዊ ተቋማት ላይ መሳተፍ እንዲሁም በፖለቲካ ህይወት በንቃት መሳተፍ ያካትታል።

ግብር/ታክስ መክፈል ሌላው ለኣውስትራሊያ ማህበረሰብ በቀጥታ ኣስተዋፅኦ የምታበረክትበት ጠቃሚ መንገድ ሲሆን ይህም ህጋዊ ግዴታ ነው። ግብር ማለት ከምታገኘው ገንዘብ የሚከፈል ይህም ማለት ከቅጥር ሥራ፣ ንግድ ሥራ፣ ወይም ከመዋዕለ ነዋይ ፍሰት የሚገኝ ሆኖ በአውስትራሊያ ግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት የሚሰበሰብ ገንዘብ ነው። ከተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጥ እና አገልግሎት የሚገኝ ግብርም አለ። ATO ሁሉም ዜጎች ስለ ታክስ መብትና ግዴታቸው እንዲያውቁና መክፈል የሚገባቸው ትክክለኛ ታክስ እንዲከፍሉ ያስተምራል።

ኣውስትራሊያውያን ብዙ ጥቅማ ጥቅሞች በታክስ ስርዓቱ በኩል ያገኙታል። ታክስ እንደ ጤና፣ ትምህርት፣ መከላከያ፣ መንገድ፣ ባቡርና ማህበራዊ ዋስትና የመሳሰሉት በመንግስት የሚታገዙ ኣገልግሎቶች ላይ ይውላሉ።

ስራ በመስራትና ታክስ በመክፈል ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ጠቃሚ ኣገልግሎቶችን ለኣውስትራሊያ ማህበረሰብ ይረዳሉ። መንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደሮች እንዲሁም የኣካባቢ ምክር ቤቶች ወጭያቸውን ለመሸፈን ታክስ ይሰበስባሉ። እነዚህ ኣገልግሎቶች ኣውስትራሊያ ሰላማዊና የበለፀገች ኣገር እንድትሆን ይረዷታል።



# ክፍል ሶስት

# መንግስትና ህግ በኣውስትራሊያ

# መንግስትና ህግ በኣውስትራሊያ

በዜግነት ስነስርዓቱ ላይ የኣውስትራሊያ ህግ ለመጠበቅና ለመታዘዝ ቃል ይገባሉ። የአውስትራሊያ መንግሥታዊ አሠራር የፓርሊያመንታዊ የዲሞክራሲ ስዓት ነው። በፓርላማዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓተ መንግስት ህግ እንዴት እንደሚወጣ፣ እንዴት እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል ለማወቅ በጣም ይጠቅምዎታል። እንደ ኣንድ ዜጋ በሃገሪቱ በማስኬድ ደረጃ ስለሚኖርዎት ሚና በሚገባ መረዳትም ጠቃሚ ነው።

## እኔ እንዴት ልደመጥ እችላለሁ?

### ድምፅ መስጠት

በክፍል 2 እንደተመለከተው፣ እድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነው ማናቸውም የኣውስትራሊያ ዜጋ በፌደራል፣በመንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደሮች ድምፅ መስጠትና የህገ መንግስት ለውጥ ሲኖር በሪፈረንዶም መሳተፍ ግዴታ ነው።

ባኣውስትራሊያ ፓርላማዊ ዲሞክራሲ ዜጎች ወኪሎቻቸውን ወደ ፓርላማ በመምረጥ ኣውስትራሊያ እንዴት እንደምትተዳደር ይወስናሉ። በትክክል ካልተመዘገቡ በምርጫ ሰዓት ድምፅዎን መስጠት ኣይችሉም።

በአውስትራሊያ ምርጫዎች ድምፅ መስጠት ግዴታ ነው፤ በተለይም በህገመንግስት ለውጥ ህዝበ-ውሳኔ በሚኖርበት ጊዜ።

የኣውስትራሊያ የምርጫ ኮሚሽን (AEC) የጋራ ብልፅግናው ወኪል ፅ/ቤት ሆኖ የፌደራል ምርጫና ሪፈረንደም ለማካሄድ ሃላፊነት የተሰጠው የጋራ ብልፅግናው የምርጫ ኣስፈፃሚ ባለ ስልጣን ነው። AEC ከመንግስት ነፃ የሆነ ተቋም ነው። የመንግስት ባለስልጣናትም ሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች በ AEC ላይ ምንም ዓይነት ተፅእኖ ኣይኖራቸውም።

በኣውስትራሊያ ድምፅ የሚሰጠው በምስጢር የድምፅ መስጫ ሳጥን ሲሆን እርስዎ ለሚፈልጉት እጩ በነፃነትና በኣስተማማኝነት መስጠት ይችላሉ። በእርስዎ ምርጫ ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው እርስዎ የመረጡትን እጩ የማወቅ መብት የለውም። በምርጫ ጊዜ ኣለ በቂ ምክንያት ድምፅዎን ካልሰጡ የገንዘብ ቅጣት ያገኛሉ። በኣስገዳጅ ምርጫ ዜጎች በፓርላማ ደረጃ ወክሎ የሚያስተዳድራቸውን ሰው የሚመርጡበት የምርጫ ስርዓት ነው።

### በወኪሎችዎ በኩል ጉዳዮችን ማንሳት

የኣውስትራሊያ ዜጎች ከወኪሎቻቸው ጋር ስለሚያሳስቧቸው የመንግስት ፖሊሲዎች ለመወያየት ሊያነጋግሯቸው ይችላሉ። በዚህ መንገድ ሁሉም የኣውስትራሊያ ዜጎች ህግና ፖሊሲዎችን በማውጣት ረገድ የራሳቸው ሚና ይኖራቸዋል ማለት ነው። ኣንድ ዜጋ ኣንድ ህግ እንዲቀየር ከፈለገ ለተመራጩ ወኪል መቀየር ስላለበት ኣንቀፅ/ህግ ሄዶ ካናገረው በኋላ ወኪሉ የቀረበውን ጥያቄ ተገቢውን ግምት መስጠት ይኖርበታል።

# ስርዓተ መንግስታችን እንዴት ተቋቋመ?

## ፌደሬሽን

ከብሪታንያ ሰዎች መስፈር በኋላና ከ1901 ዓ.ም በፊት፣ አውስትራሊያ ከስድስት የተለያዩና በራስ ከሚተዳደሩ የብሪቲሽ ቅኝ ግዛቶች የተሰራች ነበር፡፡

በእያንዳንዱ ቅኝ የግዛት ክልል የራሱ የሆነ ህገ-ደንብ መተዳደሪያ እና ከራሱ ህጎች ጋር የተዛመደ የመከላከያ፣ ኢሚግሬሽን፣ የፖስታ አገልግሎት፣ ንግድና ትራንስፖርት ነበራቸው፡፡ ነገር ግን ይሄ በያንዳንዱ ቅኝ ግዛቶች ችግር ፈጠረ፡፡ ለምሳሌ በቅኝ ግዛቶች መካከል ንግድና መጓጓዣ በጣም ውድና ከመሆኑም በላይ ፈጣንም አልነበረም፡፡ በድንበሮች ዙሪያ ህጉን ለማስከበር አስቸጋሪ ነበር፡፡ እንዲሁም በተለያዩየቅኝ ግዛቶች የመከላከያ አሰራር ዘዴያቸው የተዳከመ ነበር፡፡

በዚህም ምክንያት ሰዎች ከተለያዩ ኮሎኒዎች ይልቅ በኣንድ ሃገር ውስጥ መጠቃለልን መረጡ፡፡ በዋናነት የኣውስትራሊያ ብሄራዊ ኣንድነት መገንባት ጀመረ፡፡ የስፖርት ቡድኖች አውስትራሊያን በዓለም አቀፍ መወከል ጀመሩ፣ እንዲሁም የኣውስትራሊያ ባህል በታዋቂ ዘፈኖች፣ ግጥሞች፣ ታሪኮችና ስነጥበባት እያደገ መጣ፡፡

አገሪቷን ወደ አንድነት ለማምጣት አስቸጋሪ ተግባር ቢሆንም ከጊዜ በኋላ ግን የአንድ አውስትራሊያ አገር ምስረታ ሀሳብ እውን ሆነ፡፡ ጥር 1 ቀን 1901 ዓ.ም የቅኝ ግዛቶች በመጣመር የፈደሬሽን መስተዳድር ግዛቶችን ሲመሰርቱ ይህም የአውስትራሊያ የጋራ ብልፅግና /Commonwealth of Australia/ ተባለ፡፡


## የኣውስትራሊያ ህገ መንግስት

*Commonwealth of Australia Constitution Act 1900* (የኣውስትራሊያ ህገ መንግስት) የኣውስትራሊያ መንግስት መሰረታዊ ህጎችን ያካተተ ህጋዊ ሰነድ ነው፡፡ የአውስትራሊያ ህገ መንግሥት በመጀመሪያ እንደ ብሪታንያ ደንብ 1900 ኣንድ ክፍል ሆኖ ነበር ያለፈው፡፡ ጥር 1 ቀን 1901 ዓ.ም የኣውስትራሊያ ህገ መንግሥት ራሱን ችሎ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ የአውስትራሊያ ቅኝ ግዛቶች ወደ አንድ ነፃ ሃገር በመሆን የአውስትራሊያ የጋራ ብልፅግና ተባለ፡፡

የአውስትራሊያ ህገ መንግሥት በኮመንዌልዝ አውስትራሊያ ፓርላማ በኩል ሲመሰረት፣ የህዝብ ተወካዮችንና የህግ መወሰኛ ምክር ቤት እካላትን አቋቋመ፡፡ ህገ መንግሥቱ የአውስትራሊያን ህጎች በመተርጎም ተግባር ላይ ስልጣን ያለው የአውስትራሊያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ኣቋቋመ፡፡

የኣውስትራሊያ ህዝብ የኣውስትራሊያን ህገ መንግስት በሪፈረንደም ድምፁን በመስጠት ህጉን መቀየር ይችላል፡፡ በ1967 የኣቦሪጂን ህዝቦች በ ህዝብ ቆጠራ ይካተቱ ወይስ ኣይካተቱ ተብሎ በተደረገው ሪፈረንደም 90 በመቶ ኣውስትራሊያውያን ይካተቱ ብሎ እንደወሰነው ዓይነት ማለት ነው፡፡

ህገ መንግስት ለመቀየር የሚያስችለው የሪፈረንደም ድምፅ እጥፍ ኣብላጫ /double majority/ ድምፅ መገኘት ኣለበት፡፡ ይህም ማለት የድምፅ ሰጭዎች ኣብላጫ፣ ኣብላጫ ህዝብ ባላቸው መንግስታትና በሃገሪቱ በጠቅላላ ያሉት ድምፅ ሰጭዎች ለውጡን ደግፈው ድምፅ መስጠት ኣለባቸው፡፡




የኣውስትራሊያ ህገ መንግስት

# የመንግስት ስልጣን እንዴት መቆጣጠር ይቻላል?

አንድ ሰው ወይም ቡድን ስልጣኑን እንዳይቆጣጠረው የአውስትራሊያ ሕገ-መንግስት የመንግስትን ሥልጣኑን ሕግ አውጪ(ምክርቤት)፣ ሕግ ፈፃሚ (ለምሳሌ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እና ካቢኔው) እና ሕግ ተርጓሚ (ዳኞች) በማለት ይከፍለዋል።

## የህግ ኣውጭው ስልጣን

የህግ ኣውጭው ስልጣን ህግ የማውጣት ስልጣን ኣለው። ፓርላማ ህግ የማውጣትና የማሻሻል ስልጣን ኣለው። ፓርላማ በኣውስትራሊያ ዜጎች የተመረጡተውካዮች የተመሰረተ ነው።

## የህግ ኣስፈፃሚው ስልጣን

የህግ ኣስፈፃሚው ስልጣን ማለት ህጉን በተግባር የሚያስፈፅም ሃይል ነው። ሕግ ፈፃሚው አካል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የአውስትራሊያ መንግስት ሚኒስትሮችእና ዋናው አገረ-ገዢን ያጠቃልላል።

## የህግ ተርጓሚው ስልጣን

ዳኞች ህጉን የመተርጎምና ስራ ላይ የማዋል ስልጣን አላቸው። ፍርድ ቤቶችና ዳኞች ከፓርሊያመንትና ከመንግሥት ተጽእኖ ነጻ ናቸው።

እነዚህ ስልጣናት በአውስትራሊያ ህገ መንግሥት ውስጥ ተደንግገዋል።

# የአውስትራሊያ ርእሰ ብሄር ማን ነው?

የአውስትራልያ ርእሰ-መንግስት የአውስትራልያ ንጉሥ/ King of Australia; ግርማዊ ንጉሥ ቻርልስ III/ His Majesty King Charles III ሣልሳዊ ናቸው።


የአውስትራሊያ ንጉሥ/King of Australia በአውስትራሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር በሚሰጣቸው ምክር መሰረት የጠቅላይ ገዥውን ወኪል አድርጎ ሾሞታል። ጠቅላይ ገዥው ከማንም የፖለቲካ ቡድኖች ነጻ በሆነ መልኩ ይሰራሉ። ንጉሡ/King በመንግስት ውስጥ የቀን ተቀን የማድረግ ሚና የለውም።

በየአስተዳደር ግዛቶቹ ውስጥ ከጠቅላይ ገዥው ጋር በሚመሳሰል ድርሻ ንጉሡን የሚወክል አገረ ገዢ አለ።

## ህገመንግስታዊ የንግስና ስርዓት

አውስትራልያ ህገ መንግስታዊ ንጉሳዊ አገዛዝ ሲሆን ይህም ማለት ንጉሡ የአውስትራሊያ ርእሰ መስተዳድሮች ሲሆን፤ ነገር ግን በህገ መንግስቱ መሰረት እርምጃ መውሰድ አለበት። ንጉሡ በአውስትራሊያ እንደማይኖር ሁሉ ስልጣኖቹ ለአውስትራሊያ ጠቅላይ ገዥው ይተላለፋል።

የኣውስትራሊያ ፓርላማዊ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የብሪታንያና የሰሜን ኣሜሪካ የዲሞክራሲ ባህል የሚያንፀባርቅ ግን ደግሞ ለኣውስትራሊያ በሚያመች ሆኖ የተቀረፀ ህገ መንግስት ነው። በአውስትራሊያ አሰራር ዘዴ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የአውስትራሊያ መንግሥት መሪ ናቸው።



ግርማዊ ንጉሥ ቻርልስ III/His Majesty King Charles III

## የጠቅላይ ገዥው የሥራ ድርሻ

ጠቅላይ ገዥው የመንግስቱ ኣካል ስላልሆነና ገለልተኛ ሆኖ መስራት ኣለበት።

የጠቅላይ ገዥው ሚናዎች የሚከተሉት ናቸው፥

- የኣውስትራሊያ ፓርላማ ያፀደቃቸውን የህግ ረቂቆች ላይ ይፈርማሉ። (ይህም ንጉሳዊ ስምምነት/ Royal Assent/) ይባላል
- የክብር ተግባራትን ያከናውናሉ
- እንደ ሚንስትሮች፣ ፌደራል ዳኞች፣ እንዲሁም የሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናት ስልጣን ያፀድቃሉ
- የፌደራል ምርጫ ሂደት ያስጀምራሉ
- የኣውስትራሊያ የመከላከያ ሃይል ጠቅላይ ኣዛዥ ሆነው ይሰራሉ።

እንዲሁም ጠቅላይ ገዥው የሚባል በተለየ ሁኔታ ላይ የሚያገለግሉ " ተጠባባቂ ሃይል /'reserve powers'/ የሚባል ሃይል ኣላቸው።

# የአውስትራሊያ መሪዎች እነማን ናቸው?

### ርእሰ ብሄር
የአውስትራሊያ ንጉሥ/King of Australia

### ጠቅላይ ገዢ
የኣውስትራሊያ ርእሰ ብሄር ተወካይ

### ገዢ
በኣውስትራሊያ የተለያዩ መንግስታዊ ኣስተዳደሮች
የኣውስትራሊያ ርእሰ ብሄር ተወካይ

### ጠቅላይ ሚኒስቴር
የኣውስትራሊያ መንግስት መሪ

### የበላይ ሚንስትር /Premier
የመንግስታዊ /state ኣስተዳደር መሪ

### ዋና ሚንስቴር /Chief Minister
የክልላዊ/ territory ኣስተዳደር መሪ

### የመንግስት ሚንስትር
ኣንድን የመንግስት ኣካባቢ ለመምራት በመንግስት የተመረጠ የፓርላማ ኣባል

### የፓርላማ ኣባል (MP)
ሕዝብን የሚወክል ተመራጭ በአውስትራሊያው ምክር ቤት ወይም የመንግስት ምክር ቤት

### የህግ መወሰኛ ምክር ቤት ኣባል
በአውስትራሊያ ፓርላማ ውስጥ ለመንግስታዊ ወይም ክልላዊ ኣስተዳደር ወክሎ የተመረጠ ኣባል

### ከንቲባ ወይም የገጠር የአካባቢ ፕረዚደንት
የኣካባቢ የመንግስት ኣስተዳደር መሪ

### የኣካባቢ ምክር ቤት ተወካይ
የተመረጠ የኣካባቢ ምክር ቤት ኣባል

# ኣውስትራሊያ እንዴት ነው የምትተዳደረው?

## የኣውስትራሊያ መንግስት

የኣውስትራሊያ መንግስት፤ የጋራ ብልፅግናው የፌደራል መንግስት /Federal Government or the Commonwealth Government/ ተብሎም ይጠራል። መንግስቱ የተመሰረተው በኣውስትራሊያ የፓርላማ ኣባላት ሲሆን፤ ፓርላመንቱ ሁለት ምክር ቤቶች ኣሉት፥

- የተወካዮች ምክር ቤት
- የህግ መወሰኛ ምክር ቤት።

በፌደራል ምርጫ ኣውስትራሊያውያን ለሁለቱም የፓርላማ ምክር ቤቶች ድምፃቸውን ይሰጣሉ።

## የተወካዮች ምክር ቤት

የተወካዮች ምክር ቤት ከሁለቱ የፓርላማ ምክር ቤቶች ኣንዱ ነው። የዚህ ምክር ቤት የታችኛው ምክር ቤት /the Lower House/ ወይም የህዝብ ምክር ቤት /People's House/ በመባል ይጠራል።

ኣውስትራሊያ በተለያዩ የፌደራል የምርጫ ክልሎች ተከፋፍላለች። የፓርላማ ኣባላት የየምርጫ ክልሉ ተወካዮች ናቸው።

የተወካዮች ምክር ቤት ኣባላት ብዛት የሚወሰነው በመንግስታዊ ወይም በክልላዊ ኣስተዳደሩ ውስጥ ባለው የህዝብ ብዛት መጠን ነው። በኣጠቃላይ 150 የተወካዮች ምክር ቤት ኣባላት ኣሉ።

የህዝብ ተወካዮችና የህግ መወሰኛ ምክር ቤት ኣባላት ለመፅደቅ በሚቀርቡ ኣዳዲስ የህግ ኣንቀፆች ላይ ይከራከራሉ። የተወካዮች ምክር ቤት ለመፅደቅ በሚቀርቡ ኣዳዲስ የህግ ኣንቀፆች ላይ ይከራከራሉ፣ ድምፅ ይሰጣሉ እንዲሁም ሃገራዊ ፋይዳ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ይወያያሉ።



የተወካዮች ምክር ቤት

## የህግ መወሰኛ ምክር ቤት/The Senate

የህግ መወሰኛ ምክር ቤት ሁለተኛው የኣውስትራሊያ ምክር ቤት ነው። የህግ መወሰኛው ምክርቤት /The Senate/ ላይኛው ምክር ቤት ወይም ገምጋሚው/ Review ወይም የመንግስት ምክር ቤት /States' House/ ይባላል። በየመንግስታዊ ኣስተዳደሩ ያሉት ድምፅ ሰጭዎች የመንግስት ምክር ቤት ተወካዮቻቸውን ይመርጣሉ። የተለያየ የህዝብ መጠን ቢኖራቸውም እያንዳንዱ መንግስታዊ ኣስተዳደሮች በእኩል ቁጥር ይወከላሉ። በኣጠቃላይ 76 የህግ መወሰኛ ምክር ቤት ኣባላት ይኖራሉ። እያንዳንዱ መንግስታዊ ኣስተዳደር/ state 12 ሴኔተሮች ይኖሩታል ፤ የኣውስትራሊያ ዋና ከተማና ሰሜን ኣውስትራሊያ ክልላዊ ኣስተዳደሮች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ሴኔተሮች ይመርጣሉ።

ሴኔተሮች ኣዲስ ህግ ሲወጣ ወይም የነበረው ህግ ሲሻሻል ይመረምራሉ፣ ይከራከራሉ ድምፅ ይሰጣሉ፤ እንዲሁም ሃገራዊ ፋይዳ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ይመክራሉ።



የህግ መወሰኛ ምክር ቤት/The Senate

## መንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደሮች

በአውስትራሊያ ዋናው መሬት ስድስት መንግስታዊና ሁለት ክልላዊ ኣስተዳደሮች አሉ። እያንዳንዱ መንግስታዊ ኣስተዳደር የየራሱ ፓርላማ ኣለው። መንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደሮቹ በየራሳቸው ዋና ከተማ ውስጥ ሆነው ይሰራሉ። የመንግስታዊ ኣስተዳደር መሪ ፕሪሚየር/ የበላይ ሚንስትር ሲባል የክልላዊ ኣስተዳደሮቹ መሪ ደግሞ ቺፍ ሚንስትር/ዋና ሚንስትር ይባላል።

የአስተዳደር መንግሥታት የሚሰሩት ልክ ከአውስትራሊያ መንግሥት ጋር በሚመሳሰል መንገድ ነው። ለእያንዳንዱ አስተዳደር ክልል አንድ አገረ ገዥ የአውስትራሊያን ንጉሥ/ King of Australia ይወክላል። በሰሜናዊ ኣውስትራሊያ ክልላዊ ኣስተዳደር በጠቅላይ ገዢው የተሾመ ኣስተዳዳሪ ኣለ። የኣስተዳዳሪው ሚናና ሃላፊነት ከመንግስታዊ ኣስተዳደር ገዢ ጋር ተመሳሳይ ነው።

መንግስታዊ ኣስተዳደሮች በህገ መንግስቱ እውቅና ያገኙ ሲሆን ክልላዊ ኣስተዳደሮች ግን ኣይደሉም። መንግስታዊ ኣስተዳደሮች በራሳቸው ህግ ማፅደቅ የሚችሉ ሲሆን የራስ ገዝ ክልሎች ህግ ግን በኣውስትራሊያ መንግስት በኩል በማናቸውም ጊዜ ሊለወጥ ወይም ሊፋቅ ይችላል።

በመንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደሮች ምርጫ፣ የኣውስትራሊያ ዜጎች በኣካባቢያቸው ወኪሎቻቸውን ለመምረጥ ድምፅ ይሰጣሉ። እነዚህ ተወካዮች የሚመለከተው መንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደር ፓርላመንት ይሆናሉ።

## የኣካባቢ ኣስተዳደር

መንግስታዊ ኣስተዳደሮችና የሰሜን ኣውስትራሊያ ክልላዊ ኣስተዳደር በተለያዩ የኣካባቢ መስተዳድሮች የተከፋፈሉ ናቸው። እያንዳንዱ ኣካባቢ የራሱ የሆነ ምክር ቤት ኣለው። ምክር ቤቶች ለኣካባቢው ማህበረሰብ ኣስፈላጊ የሆኑ ኣገልግሎቶች የማቀድና የማቅረብ ሃላፊነት ኣለባቸው። በኣካባቢው የሚኖሩት ዜጎች ምክር ቤታቸምን የሚመሩ ሰዎች ለመምረጥ ድምፅ ይሰጣሉ።

# እነዚህ ሶስት የመንግስት እርከኖች ምን ያደርጋሉ?

ምንም እንኳን የነዚህ ሶስት የመንግስት የሃላፊነት መደራረቦች ቢኖሩም ፤ ሶስቱም የመንግስት የኣስተዳደር እርከኖች የየራሳቸው የሆነ ልዩ ልዩ ኣገልግሎቶች ይሰጣሉ።

**የኣውስትራሊያ መንግስት የሚከተሉትን ተቋሞች በሃላፊነት ይመራል፤**

የግብር/የታክስ
የብሄራዊ የኢኮኖሚ ኣመራር
የስደትና ዜግነት ጉዳይ
የስራ ቅጥር ድጋፍ
የፖስታ ኣገልግሎትና የመገናኛ መረብ
ማህበራዊ ደህንነት (የጡረታና የቤተሰብ እገዛ)
መከላከያ
ንግድና ግብይት
ኣየር ማረፊያዎችና የበረራ ደህንነት
የውጭ ጉዳይ( ከሌሎች ኣገሮች ያለው ግንኙነት)።

**የመንግስት እና የክልል ኣስተዳደሮች የመጀመሪያ ኃላፊነታቸው የሚከተለው ነው፤**

ሆስፒታሎችና የህክምና ኣገልግሎቶች
ትምህርት ቤቶች
መንገዶችና የባቡር መስመሮች
ደኖች
የፖሊስና የኣምቡላንስ ኣገልግሎቶች
የህዝብ መጓጓዣዎች።

**የኣካባቢ ኣስተዳደሮች( የኣውስትራሊያ ዋና ከተማ ክልላዊ ኣስተዳደር ጨምሮ) የሚከተሉትን ተቋማት በሃላፊነት ይመራሉ፤**

የመንገድ ምልክቶች፣ የትራፊክ መቆጣጠሪያዎች
የውስጥ መንገዶች፣ የእግረኛ መንገዶች፣ድልድዮች
ማፋሰሻዎች
ፓርኮች የህፃናት መጫወቻ ስፍራዎች፣ መዋኛ ስፍራዎች፣የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች
ጊዚያዊ ሰፈሮችና የተጓዦች ማረፊያ ሰፈሮች
የምግብና የስጋ መመርመሪያዎች
የድምፅና የእንስሳት ቁጥጥር
የቆሻሻ ማሰባሰቢያ
ኣብያተ መፃህፍት፣ ኣዳራሾች፣ የማህበረሰብ ማእከላት
የህፃናትና የኣረጋውያን የእንክብካቤ ማእከላት
የግንባታ ፈቃድ
ማህበራዊ እቅድ
የኣካባቢው ምህዳራዊ ጉዳዮች።

# የኣውስትራሊያ ፖለቲካ ፓርቲዎች በኣውስትራሊያ ኣስተዳደር ምን ዓይነት ሚና ኣላቸው?

የፖለቲካ ፓርቲ ማለት ስለ ኣንድ ሃገር አስተዳደራዊ ዘዴ ተመሳሳይ ኣስተሳሰብ ያላቸው ሰዎችን ያሰባሰበ ቡድን ነው። የፓርቲ ሃሳባቸው ወደ ህግ እንዲቀየር ጠንክረው በጋራ ይሰራሉ። የኣውስትራሊያ ዋና ዋና የፖለቲካ ፓርቲዎች፤የኣውስትራሊያ ለዘብተኛ ፓርቲ /Liberal Party of Australia/፣ የኣውስትራልያ የሰራተኞች ፓርቲ /Australian Labor Party/፣ ብሄራዊ ፓርቲ /the Nationals/ እና የኣረንጓዴው ፓርቲ /the Australian Greens/ ናቸው።

ኣብዛኞቹ የፓርላማ ኣባላት የፖለቲካ ፓርቲ ኣባላት ናቸው። ጥቂቶቹ የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ኣባላት ኣይደሉም እነዚህም ነፃ ተወዳዳሪዎች /independents/ ይባላሉ

በኣውስትራሊያ ሰዎች እስከፈለጉት ድረስ የፖለቲካ ፓርቲ ኣባል መሆን ይችላሉ።

# የኣውስትራሊያ መንግስት እንዴት ነው የሚቋቋመው?

የኣውስትራሊያ መንግስት በኣጠቃላይ የሚቋቋመው የፌደራሉ ምርጫ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ በኣሸናፊው ፓርቲ ወይም በፓርላማ ውስጥ ከፍተኛ የተወካዮች ቁጥር ባላቸው ፓርቲዎች ቅንጅት ነው። የኣሸናፊው ፓርቲ መሪ የኣውስትራሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናል።

የፌደራል ምርጫው ከተጠናቀቀ በኋላ፤ በተወካዮች ምክር ቤት በሁለተኛ ደረጃ ያሸነፈው ፓርቲ ወይም የፓርቲዎች ቅንጅት የመንግስቱ ተቃዋሚ/ተፎካካሪ ይሆናል። የዚህም መሪ የተቃዋሚ መሪ ተብሎ ይጠራል።

የኣውስትራሊያው ጠቅላይ ሚኒስትር ከተወካዮችና ከመንግስት ምክርቤቶች ኣውጣጥቶ በኣውስትራሊያ መንግስት ሚኒስትርነት እንዲያገለግሉ በእጩነት ያቀርባል። ጠቅላይ ገዢው በጠቅላይ ሚኒስትሩ የቀረበላቸውን የሚኒስትሮች ሹመት ያፀድቃሉ።

የመንግስት ሚኒስትሮች ለኣንድ የመንግስት የስራ ዘርፍ (ፖርቶፎሊያ) ለምሳሌ የስራ ቅጥር፣ የኣገር ተወላጆች ጉዳይ፤ ወይም የገንዘብ ሚንስቴር በሃላፊነት ይመራሉ። ከፍተኛ የስራ ድርሻ ያላቸው ሚኒስትሮች ካቢኔ ይመሰርታሉ ካቢኔው የሃገሪቱን ቁልፍ ውሳኔ የሚወስን የመንግስት ኣካል ይሆናል።

# ህግ እንዴት ይወጣል?

የኣውስትራሊያ ፓርላማ ሃገሪቱን የሚጠቅሙ ህግጋት ያወጣል ወይም ያሻሽላል።

ኣንድ የኣውስትራሊያ የፓርላማ ኣባል ኣንድ ኣዲስ ህግ ቢያቀርብ ወይም ባለው ህግ ላይ የሚያቀርበው የማሻሻያ ሃሳብ ‘ረቂቅ ህግ/ Bill’ይባላል።

የህዝብ ተወካዮችና የህግ መወሰኛው ምክር ቤቶች የሚቀርበውን የህግ ረቂቅ ይመረምራሉ፣ ይከራከሩበታል በመጨረሻም ድምፅ በመስጠት ያሳልፉታል ወይም ይጥሉታል።

የህግ ረቂቁ በሁለቱም ምክር ቤቶች ዘንድ ኣብላጫ ድምፅ ካገኘ ወደ ጠቅላይ ገዢው ያልፋል።

ጠቅላይ ገዢው ከፈረሙበት በኋላ ህግ ይሆናል። ይህም ‘ንጉሳዊ ስምምነት/Royal Assent’ይባላል።

መንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደሮች በተመሳሳይ መንገድ ህግ ያወጣሉ።




# ህግ እንዴት ይከበራል?

## ፍርድ ቤቶች

በኣውስትራሊያ ያሉት ፍርድ ቤቶች ነፃ ናቸው። ፍርድ ቤቶች ኣንድ ግለሰብ ህግ መጣስ ኣለመጣሱን መርምረው ውሳኔ ይሰጡበታል። ፍርድ ቤቶች በቀረበላቸው ማስረጃ መሰረት ነው ውሳኔ የሚሰጡት።

## ዳኞችና የአጥቢያ ዳኞች

ዳኞች ወይም አጥቢያ ዳኞች በፍርድ ቤት ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን እርከኖች ናቸው። ዳኞችና አጥቢያ ዳኞች የማንም ተጽእኖ የሌለባቸውና ምን መወሰን እንዳለባቸው ማንም ሊነግራቸው አይችልም።

ዳኞችና የአጥቢያ ዳኞች የሚመረጡት በመንግሥት ሲሆን ባቀረቡት ውሳኔ ላይ ካልተስማማ መንግሥት ከሥራ ማሰናበት አይችልም።

## የፍርድ ሸንጎ

በኣውስትራሊያ የህግ ስርዓት ማንኛውም ሰው በፍርድ ቤት ጥፋተኛ መሆኑ እስካልተወሰነበት ድረስ ወንጀለኛ ኣይደለም። ማንኛውም ሰው በፍርድ ቤት በህግ ባለሞያ የመወከል መብት ኣለው።

ፍርድ ቤት ፍርድ ሸንጎዎችን በመጠቀም ህግ የሚጥሱትን ሰዎች ጉዳይ ውሳኔ ለመስጠት ይጠቀማል። የፍርድ ሸንጎ ሚና ኣንድ ሰው ጥፋተኛ ወይም ከወንጀል ነፃ መሆኑን በፍርድ ቤት ፊት መወሰን ነው። የፍርድ ሸንጎ ከህዝብ ውስጥ በነሲብ/በዘፈቀደ የሚመረጡ ተራ የኣውስትራሊያ ዜጎች ስብስብ ነው። ዳኛው ለፍርድ ሸንጎው የህግ መግለጫ ይሰጣል። በወንጀል ምርመራ ኣማካኝነት ፍርድ ሸንጎው ኣንድ ግለሰብ ጥፋተኛ ሆኖ ካገኘው ዳኛው ቅጣቱን ይወስናል።

## ፖሊስ

ፖሊስ በማህበረሰብ ውስጥ ስርዓትና ሰላም ያስከብራል። የህዝብ ህይወትና ንብረት መጠበቅ ተግባራቸው ነው። ከመንግስት ጣልቃ ገብነት ነፃ ነ ናቸው። ፖሊስ ኣንድ ሰው ህግ ጥሷል ብሎ ካመነ ኣስሮ ወደ ፍርድ ቤት የማቅረብ ሃላፊነት ኣለው። ፖሊስ ለፍርድ ቤት ማስረጃ ያቀርባል ነገር ግን ፍርድ ቤቱ ነው ሰውየው ጥፋተኛ መሆን ኣለመሆኑን የሚወስነው።

ሁሉም መንግስታዊ ኣስተዳደሮችና የሰሜን ኣውስትራሊያ ክልላዊ ኣስተዳደር የራሳቸው የፖሊስ ኃይል ኣላቸው። በሁሉም መንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደሮች የሚከሰቱ የወንጀል ተግባራትን ይከላከላል።

ኣውስትራሊያም፣ የኣውስትራሊያ ፌደራል ፖሊስ (AFP) የሚባል ብሄራዊ የፖሊስ ሃይል ኣላት። የኣውስትራሊያ ፌደራል ፖሊስ(AFP) የፊደራል ህጎችን የሚጥሱ እንደ የእፀ ዝውውር፣ ለሃገራዊ ደህንነት የሚያሰጉ ወንጀሎችን፣ እንዲሁም ኣካባቢውን የሚጎዱ ወንጀሎች ላይ ኣተኩሮ ይሰራል። AFP በኣውስትራሊያ ዋና ከተማ ክልላዊ ኣስተዳደርም ጠቅላላ የፖሊስ ስራ ይሰራል።

በኣውስትራሊያ ፖሊስና ህብረተሰቡ ጥሩ ግንኙነት ኣላቸው። እርስዎ ያዩት ወንጀል ካለ ለፖሊስ በማመልከት ከኣካባቢዎ ፖሊስ እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።

በኣውስትራሊያ ለፖሊስ ጉቦ መስጠት በጣም ከባድ ወንጀል ነው። ለፖሊስ ኣባል ጉቦ መስጠት በራሱ ወንጀል ነው።

## ወንጀሎች በኣውስትራሊያ

ከኣውስትራሊያ ህጎች ጋር ራስዎን ማስተዋወቅ ጠቃሚ ነው። በኣውስትራሊያ ባለማወቅ ህግ ጥሰው ቢገኙ ኣለማወቅዎ ከመከሰስና ከመቀጣት ኣያድንዎትም።

ማንኛውም ሰው ከቤተሠቡ፣ ጓደኞቹ እና ፍቅረኛው ጋር ጠቃሚ እና አስተማማኝ የሆነ ተሞክሮ እና ትስስር የመፈፀም መብት አለው። በጣም ከባድ ከሆኑት አንዳንድ ወንጀሎች ውስጥ የሚካተቱት፤ የነብስ ግድያ፣ ድብደባ፣ የወሲባዊ ጥቃት፣ በሰውም ሆነ በንብረት ላይ ጥቃት ማድረስ፣ በመሳሪያ የታገዘ ዘረፋና ስርቆት፣ ለኣቅመ ኣዳም ባልደረሱ በታዳጊዎችና ህጻናት ላይ የወሲብ ጥቃት መፈፀም፣ ኣደገኛ የተሽከርካሪ ኣነዳድ፣ ህገ-ወጥ የሆኑ አደገኛ እጾችን መያዝና ማጭበርበር።

በሌሎች ኣገሮች እንዳለው በኣውስትራሊያም በሌላ ሰው ላይ ጥቃት መፈፀም ህገ ወጥና በጣም ከባድ ወንጀል ነው። ከነዚህም ውስጥ በቤትና በትዳር ውስጥ የሚደርስ የቤት ውስጥ ጥቃት የሚባለውን ያካትታል። የቤትና የቤተሰብ ጥቃት በማስፈራራትና ለህይወታቸው ስጋት በመፍጠር ሰዎችን ለመቆጣጠር ሲባል የሚደረግ ማስፈራራትን ያካትታል። የሀገር ውስጥ እና የቤተሰብ ሁከት፤ መማታትን፣ የቤተሰብ አባልን ከጓደኛ እና ከቤተሰብ መነጠልን ወይም ሕፃናት ወይም የቤት እንስሳትን ማስፈራራትን ያጠቃልለላል። የቤት ውስጥ እና የቤተሰብ ሁከትና ጥቃት ተቀባይነት የለውም፤ ሕገወጥም ነው።

ማንኛውም ሰው በክፉ ሊስተናገድ ወይም ሊጎዳ አይገባም።

አንተ ወይም አንተ የምታውቀው ሰው አደጋ ካጋጠመው የፖሊስ እገዛ መጠየቅ ያስፈልጋል። ለበለጠ መረጃ በ www.respect.gov.au እና www.1800respect.org.au ያገኛሉ

## የትራፊክ ጥፋቶች

የመንገድና የትራፊክ ህጎች በመንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደሮች ቁጥጥር ይደረግባቸዋል። ሰዎች የትራፊክ ፖሊስ በመጣሳቸው ምክንያት ይቀጣሉ ለእስርም ሊዳረጉ ይችላሉ። በኣውስትራሊያ ተሽከርካሪ ለመንዳት የኣካባቢው መንጃ ፈቃድና የተሽከርካሪው የምዝገባ ፈቃድ የግድ ያስፈልግዎታል።

በመኪናው ውስጥ ያለው ማንኛውም ተሳፋሪ ቀበቶ የግድ መታጠቅ ኣለበት። ጨቅላዎችና ህፃናት ተገቢውን የመኪና መቀመጫ የግድ መጠቀም ኣለባቸው። የትራፊክ ህግ በጣም ጥብቅ ነው። ኣደንዛዥ እፅ ወይም ከሚገባው የኣልኮል መጠጥ ጠጥቶ ማሽከርከር ህገ ወጥነት ነው። በሚነዱበት ሰዓት ሞባይል በእጅ ይዞ ማውራት ህገወጥነት ነው።



# ምዕራፍ ኣራት

# የኣውስትራሊያ እሴቶች



# የኣውስትራሊያ እሴቶች

የኣውስትራሊያ እሴቶች ነፃነት፣ መከባበር፣ ፍትሃዊነት እና እኩል ተጠቃሚነት ሲሆኑ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ የበለፀገ እና ሠላማዊ የማሕበረሰባችን መኖሪያ ቦታ እንዲሆን ዋና መሰረቶች ናቸው።

እሴቶቻችን ሀገራችንን የሚገልፁ እና የቀረፁ ናቸው፤ ለዚህም ነው ብዙ ሰዎች የአውስትራሊያ ዜጎች ለመሆን የሚፈልጉት።

የኣውስትራሊያ ዜግነት ማለት እነዚህን እሴቶች የዕለት ተዕለት ተግባርዎ በማድረግ ከኣካባቢዎ ህብረተሰብ ጋር መኖር ማለት ነው። ስለዚህ ሁሉም የአውስትራሊያ ህዝብ እሴቶችን ማክበር፣ ማስተላለፍ እና መጠበቅ እንዳለበት መገንዘቡ በጣም ጠቃሚ ነው።

## እሴቶቻችን

### ለህግ የበላይነት ያለው ቁርጠኝነት

ሁሉም አውስትራሊያዊያን ባሉን ሕጎች እና ሕጋዊ አሰራሮች ከለላ ይደረግላቸዋል። ኣውስትራሊያውያን የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት ከመጠበቅ ኣንፃር የህግ ዋጋ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ ይገነዘባሉ።

በህግ የበላይነት መሰረት ሁሉም ኣውስትራሊያውያን በህግ ፊት እኩል ናቸው። ማንም ሰውም ሆነ ቡድን ከህግ በላይ ኣይደለም። በአውስትራሊያ እያንዳንዱ ሰው ለህጉ ተገዢ መሆን አለበት፤ በማንኛውም ጊዜ ህጉን መጣስ የለበትም፤ ካልሆነ ግን ቅጣት ይጠብቀዋል። ማንም የሚያይዎት ሰው ባይኖርም ህጉን የግድ ማክበር ይኖርብዎታል።

የኣውስትራሊያ ህግ በኣውስትራሊያ ውስጥ ላሉት ሰዎች ሁሉ ይመለከታል። ኣለ ምንም የጀርባ ታሪክ ወይም ባህል የኣውስትራሊያን ህግ የማክበር ግዴታ ኣለብዎት።

### ፓርላሜንታሪያዊ ዲሞክራሲ

የአውስትራሊያ መንግሥታዊ አሠራር የፓርሊያመንታዊ የዲሞክራሲ ስዓት ነው። ህጋችን የሚወሰነው በህዝብ በተመረጡ የፓርላማ ኣባላት ነው። ይህም ማለት የኣውስትራሊያ ዜጎች ኣገሪቱ በምትተዳደር ሂደት ተሳትፎ ኣላቸው ማለት ነው። የኣውስትራሊያ መንግስት ስልጣን የሚመጣው ከህዝቡ ነው። ምክንያቱም በፓርላማ የሚወክሏቸውን ሰዎች ድምፅ በመስጠት ይመርጣሉና።

በኣውስትራሊያ ድምፅ መስጠት ግዴታ ነው። ይህም በምርጫ ላይ የመሳተፍ ጠቃሚነት ያሳያል።

## የመናገር ነፃነት

በአውስትራሊያ የሚገኙ ሰዎች ሕጉን እስካከበሩ ድረስ ሃሳባቸውን በነፃ የመግለፅ መብት አላቸው። በአውስትራሊያ ሰዎች ማሕበራዊ ወይም ፖለቲካዊ ውይይቶችን ለመከወን በሕዝባዊ ወይም በግል ስፍራዎች በነፃነት መሰብሰብ ይችላሉ፡፡ ሰዎች ስለማንኛውም ርእስ የሚያስቡትን ነገር ከሌሎች ጋር ለመናገር፣ ለመፃፍ ወይም ለመወያየት ሙሉ ነፃነት አላቸው። ጋዜጦች፣ ቴሌቪዥን እና የሬድዮ ማሰራጫዎች አንድ ዓይነት ነፃነት አላቸው።

ኣውስትራሊያውያን መንግስት የሚያደርጋቸውን ተግባራት መቃወም ይችላሉ፤ምክንያቱም የሰላማዊ ህዝባዊ ተቃውሞን መታገስ የዲሞክራሲ አንድ ጠቃሚ ክፍል ነው።

በማናቸውም ግለሰብ ሆነ ቡድን ላይ በባህሉ፣ በዘሩ፣ በሃይማኖቱም ሆነ ጥንተ መሰረቱ ምክንያት ጥቃት ማድረስ በፍፁም ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም የኣውስትራሊያን እሴቶችና ህግን ይፃረራልና፡፡ ስም ማጥፋትም ሆነ ሌሎች ህገወጥ ስራ እንዲሰሩ ማበረታታት በራሱ ህገወጥ ነው፡፡ የሌሎች የመናገርና ራሳቸውን የመግለፅ ነፃነት የግድ መከበር ኣለበት፤ እነሱ የሚገልፁበት መንገድ ህጋዊ እስከሆነ ድረስ።

## የማህበራት ነፃነት

በህጋዊ መንገድ እስከፈፀሙት ጊዜ ድረስ በኣውስትራሊያ ሰዎች በነፃ ፍላጎታቸው ከማንኛውም ቡድን ጋር የመቀላቀልም ሆነ ለቆ የመውጣት ነፃነት ኣላቸው። ሰዎች ከማንኛውም ህጋዊ ድርጅት ማለትም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የሰራተኛ ማህበር፣ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ ማህበራዊ ቡድን ቡድን ጋር የመቀላቀል ነፃነት ኣላቸው። ግለሰቦች የአንድ ድርጅት አባል እንዲሆኑ ወይም ድርጅቱን እንዲለቁ አይገደዱም።

ኣውስትራሊያውያን ከሌሎች ጋር በነፃነት የመሰብሰብ፣ እንዲሁም መንግስት የሚያደርገውን ተግባር መቃወም ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ሁሉም ተቃውሞዎች በህጉ መሰረት መፈፀም ይገባቸዋል፡፡ ይህም ማለት የግድ ሰላማዊ መሆን ኣለበት እንዲሁም የማንንም ህይወትና ንብረት የሚጎዳ መሆን የለበትም።

## የሃይማኖት ነፃነት

አውስትራሊያ ሕጋዊ የሆነ ብሔራዊ እምነት የላትም። በአውስትራሊያ የሚገኙ ሰዎች ማንኛውን የመረጡትን ሐይማኖት መከተል ይችላሉ፡፡ ኣለ ምንም የሃይማኖትና የእምነት ልዩነት የኣውስትራሊያ መንግስት ሁሉንም ዜጎች በእኩልነት ያስተናግዳቸዋል፡፡ ቢሆንም ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች የኣውስትራሊያን ህግ የግድ ማክበር ኣለባቸው።

ሃይማኖታዊ ህጎች በኣውስትራሊያ ህግ ተቀባይነት የላቸውም፡፡ የኣውስትራሊያ ህግ በማንኛውም ሰው የግድ መከበር ኣለበት ከሃይማኖታዊ ህጎች የተለየ ቢሆንም ጭምር፡፡ ኣንዳንድ ሃይማኖቶችና ባህሎች ላይ የሚካሄዱ ልምዶች ለምሳሌ ኣንድ ሰው በኣንድ ወቅት ከብዙ ሰው ጋር የሚደረገው ጋብቻ /polygamy/ እንዲሁም የጉልበት ጋብቻ በኣውስትራሊያ ህገወጥ ተግባራት መሆናቸውና እስከ እስራት ድረስ የሚደርሱ ከፍተኛ ቅጣቶችን ያስከትላሉ።

የሃይማኖት ፅንፈኝነት በኣውስትራሊያ ተቀባይነት የለውም፡፡ የአውስትራሊያ ሕግን እስካከበሩ ድረስ ኣለምንም የዘርና የሃይማኖት ልዩነት ሁሉም ሰዎች ግባቸውና ፍላጎታቸውን ለማሳካት እኩል እድል ይሰጣቸዋል፡፡



## በሕግ ፊት ሁሉም ሰዎች እኩል ናቸው

የአውስትራሊያ ማሕበረሰብ የሁሉም ሰዎች መብት እኩልነት ያለ ፆታ፣ የፆታ ምርጫ፣ ዕድሜ፣ አካል ጉዳተኝነት፣ ሐይማኖት፣ ዘር ወይም የአገር ወይም ጎሳ ተወላጅነት ልዩነት ዋጋ ይሰጣል። ኣንድ ሰው ከሌላው ሰው በተለየ መልክ እንዳይታይ የሚከላከሉ ብዙ ህጎች ኣሉ።

ይህ ህግ የሰዎችን የኋላ ታሪክ ልዩነት መሰረት በማድረግ ኣንዱን ተጠቃሚ ሌላውን ተጎጂ ሳያደርግ በሁሉም ኣውስትራሊያ ተግባራዊ ይደረጋል። ለምሳሌ የቡድሃ እና የሌሎች እምነት ተከታዮች ከክርስቲያን እኩል ይስተናገዳሉ። በእኛ ሕግ መሰረት ሁለት ሰዎች እርስ በእርስ መጋባት ይችላሉ፤ በሁለት ወንዶች ወይም ሴቶች መካከል ጋብቻ መፈፀምን ያጠቃልላል።

በአውስትራሊያ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች እኩል መብት አላቸው። ግባቸውን እና ፍላጎታቸውን ለመፈፀም እኩል እድል ሊሰጣቸው ይገባል። ሁሉም ወንዶች እና ሴቶች እኩል የትምህርት እና የስራ ቅጥር ዕድል፣ በምርጫዎች ላይ የመምረጥ፣ ለምክር ቤት የመመረጥ፣ የአውስትራሊያ መከላከያ ሠራዊት እና የፖሊስ ኃይል አባል የመሆን እና በሕግ ፊት እኩል የመስተናገድ እድል አላቸው።

በፆታው ምክንያት ማንኛውንም ሰው ማዳላት ህገ ወጥነት ነው። በኣውስትራሊያ ሴቷ በትምህርትም ሆነ በስልጠና ከወንዱ በልጣ እስከተገኘት ቅድሚያ የስራ እድል ታገኛለች።

ሁለቱም ወንዶች ወይም ሴቶች በግል ጉዳያቸው እንደ ጋብቻና ሃይማኖት ላይ የየራሳቸው የግል ምርጫ ማድረግ ይችላሉ። ከማስፈራራትና ከዓመፀኝነትም በህግ ይጠበቃሉ። በትዳር አጋር ላይ አካላዊ ጥቃት መፈፀም በአውስትራሊያ ተቀባይነት የሌለው የወንጀል ድርጊት ነው።

ፍች መፈፀም በኣውስትራሊያ ቅቡል ነው። ከሁለት ኣንዱ በጋብቻ መቀጠል ቢፈልግም፤ መፋታት የፈለገ ባል ይሁን ሚስት የፍቺ ማመልከቻውን ለፍርድ ቤት በማቅረብ መፋታት ይችላል።

## የተጠቃሚነት እኩልነትና ፍትሃዊነት/‘fair go’

እኛ ማንም ሰው ፍትሃዊነት ይገባዋል ብለን እናምናለን። ሰዎች በማንኛውም የመደብ ልዩነት መገደብ የለባቸውም። ማንም ሰው የኋላ ታሪኩ ግምት ውስጥ ሳይገባ ሕይወቱን ያለ አንዳች ችግር እንዲመራ እኩል ዕድል የሚሠጠው፤ ማንም ሰው እኩል ሕጋዊ መብት እንዳለው ለማረጋገጥ እና የአውስትራሊያን ሕብረተሰብ ፍትሃዊነት ለማሳየት ነው።

አንድ ሰው ስኬታማ መሆን ካለበት ጠንክሮ በሚሠራው ስራ እና በተሰጥዖው መሆን አለበት። ይህም ማለት አንድ ሰው ስራ ማግኘት ያለበት በችሎታው እና በሥራ ልምዱ እንጂ በፆታው፣ በሀብቱ ወይም በጎሳው መሆን የለበትም።

ማንም ድርጅት ያለውን ክፍት ቦታ መሙላት ሲፈልግ፤ ለዛ ቦታ የተሻለ ብቃትና የስራ ልምድ ያለውን ሰው መርጦ እንዲቀጥር ህጉ ይደግፈዋል።

ወደ አውስትራሊያ የመጡ ብዙ አዲስ ስደተኞች በንግድ ሥራ፣ በሙያቸው፣ በጥበብ፣ በሕዝባዊ አገልግሎት እና በስፖርት መስክ ጠንክረው በመስራታቸው መሪዎች ሆነዋል።



## የጋራ መከባበር እና ሌሎችን መቻል

በኣውስትራሊያ የማንኛውም ግለሰብ ነፃነትና ክብር እንዲሁም ሃሳቦችና ምርጫዎችን ኣክብር፡፡

በሌላ ሰው ላይ ሁከትና ጥቃት መፍጠር ሕገወጥነት ነው፡፡ ማንኛውም ሁከት፤ ንግግርም ሆነ አካለዊ ጉንተላ ሕገወጥ ነው፡፡ አውስትራሊያውያን ግብረገብነት በተላበሰ፣ የማይጎዳ፣ ከዛቻ እና ከሁከት የፀዳ ሠላማዊ በሆነ አለመስማማት ያምናሉ፡፡

በኣውስትራሊያ የፆታ ግንኙነት ፈቃድን ኣስመልክቶ በጣም ጥብቅ ህግ ኣለ፤ እንደሚኖሩበት መንግስታዊ ኣስተዳደር ህግ 16 ወይም 17 ዓመት እድሜ ነው፡፡ ለምሳሌ የ20 ዓመት ዕድሜ ያለው ወንድ የ15 ዓመት ዕድሜ ካላት ሴት ጋር የፆታ ግንኙነት ማድረግ ኣይችልም፡፡ ምክንያቱም በኣውስትራሊያ ባሉት ሁሉም መንግስታዊና ክልላዊ ኣስተዳደሮች ያለውን ህግ የሚጥስ በመሆኑ ነው፡፡

በኣውስትራሊያ ህጋዊ የፖሊስ ተግባር መደገፍ ኣለበት፡፡ የፖሊስ ህጋዊ ጥያቄ መታዘዝ ይገባዎታል ምክንያቱም የኣውስትራሊያ ህግ ለማክበር ቃል ገብተዋልና፡፡

የጋራ መከባበርና መቻቻል ኣውስትራሊያ ትልቅ ዋጋ የምትሰጠው መርህ ነው፡፡ ይህም ማለት ሰዎች ያላቸው ሃሳብ ከርስዎ ቢለይም የነሱን ኣስተያየት ማዳመጥና ማክበር በጣም ኣስፈላጊ ነው፡፡ ሊያስማማቸው የማይችል ነገር በመሃላቸው ሲከሰት ሰዎች እርስ በበርሰ መቻቻል አለባቸው፡፡

ዘረኝነት በአውስትራሊያ ቦታ የለውም፡፡ ይህ ዘረኝነትን የሚገልፅ አስቀያሚ ነገር መፍጠር ወይም በበይነመረብ ወይም በሌሎች ህትመት መልቀቅ እና በማሕበራዊ ወይም በስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ላይ ዘረኝነት ተኮር ትችት ማቅረብን ያጠቃልላል፡፡

# ማህበረሰባችን

## እስተዋፅዖ ማበርከት

ዜግነት ለማሕበረሰባችን እ ና ለአገራችን የመኖር ዋስትና ላይ ሙሉ ተሳትፎ ለማድረግ ዕድል ይሰጣል። ይህም ማለት እንደ ማንኛውም ኣውስትራሊያዊ የማህበረሰብ ኣባል ሃላፊነትዎን ለመወጣት ዝግጁ ያደርግዎታል ማለት ነው። በኣውስትራሊያ የሚኖር ሰው ሁሉ ከህብረተሰቡ ጋር መሳተፍና ኣስተዋፅኦ እንዲያደርግ ኣውስትራሊያውያን ይጠብቃሉ። እንዲህ ማድረግ ሲችል ማንኛውም ሰው እራሱን እና ቤተሠቡን የመደገፍ ኃላፊነት አለው።

## በችግር ላይ ላሉ ሰዎች ሃዘኔታ ማሳየት

ኣውስትራሊያውያን 'ለጓደኝነት' ከፍተኛ ዋጋ እንሰጣለን። በችግር ጊዜ እርስ በርሳችን እንረዳዳለን። ለምሳሌ ይህ ምናልባት አንድ ሽማግሌ የሆነ ጎረቤትን ምግብ መስጠት፣ የሕክምና ቀጠሮ ያለውን ጓደኛ በመኪና ማድረስን ወይም የታመመ፣ ደካማ ወይም ብቸኛ የሆነ ሰውን መጎብኘት እንደ ማለት ነው።

በጓደኝነት መንፈስ ኣውስትራሊያ ጠንካራ ነፃ የማህበረሰብ ኣግልግሎት ባህል ኣላት፤ እያንዳንዱ የሚተጋገዝና ጠንካራ የማህበረሰብ ትስስርን ይፈጥራል። ነፃ ኣገልግሎት እውቀት ለማካፈል፣ ሞያ ለመማር፣ ቅንጅት ለመጨመርና በኣውስትራሊያ የኔነት ስሜት ለማጠናከር ጥሩ ኣጋጣሚ ነው። በኣውስትራሊያ የነፃ ኣግልግሎት ለመስጠት ብዙ ኣማራጮች ኣሉ።

## እንግሊዝኛ እንደ ብሔራዊ ቋንቋ

የኣውስትራሊያ ማህበረሰብ እንግሊዝኛን እንደ ብሄራዊ ቋንቋና እንደ ኣንድ የማህበረሰቡ የኣንድነት ስሜት ፈጣሪ ኣድርገው ዋጋ ይሰጡታል። በኣውስትራሊያ የሚኖሩ ሰዎች እንግሊዝኛ ለመማር ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል።

እንግሊዝኛ መናገርን መማር ለመማር፣ ስራ ለማግኘትና ከህብረተሰቡ ጋር በኣግባቡ ለመወሃድ በጣም ጠቃሚ ነው። በኢኮኖሚው ለመሳተፍና ከህብረተሰቡ ጋር ለመወሃድ ይጠቅማል። የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንግሊዝኛ ያልሆነ የአውስትራሊያ ዜግነት አመልካቾች እንግሊዝኛ ለመማር አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

## ደህንነቱ የተጠበቀ ማሕበረሰብ ለመፍጠር መርዳት

በኣውስትራሊያ ሁላችንም ኣውስትራሊያን የመከላከል ግዴታ ኣለብን። ለምሳሌ በአውስትራሊያ የሚገኙ ሰዎች ጓደኛቸው ወይም ጎረቤታቸው አደገኛ ወንጀል ለመፈፀም ማቀዱን ካወቁ ለአውስትራሊያ መንግስት ባለስልጣናት ይህን ጉዳይ ወዲያውኑ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። በዚህም መንገድ የህብረተሰባችን ደህንነት መጠበቅ እንችላለን።

መተመሳሳይ ኣንድ ህፃን በሆነ መንገድ ጥቃት ሲደርስበት ከታየ በቀጥታ ወደ ፖሊስ ሪፖርት ማድረግ ኣስፈላጊ ነው።

በበይነመረብ መስመር ላይ አፀያፊ ነገር መልቀቅ በአውስትራሊያ ተቀባይነት የለውም። ይህ እንዳንዴ የኮፒዩተር ዓለምን አለአግባብ መጠቀም ይባላል። ለምሳሌ የፆታዊ ግንኙነት ፎቶዎች ወይም ቪዲዮዎችን ከባለቤቱ ፈቃድ ውጭ በበይነመረብ መልቀቅ፣ የግለሰቦችን ሚስጥር ለማወቅ በበይነመረብ ማድባት፣ በግለሰቦች ላይ ዘረኝነት የሚገልፅ ትችት በበይነመረብ መልቀቅ። በተለያዩ መንገዶች የኮፒዩተር ዓለምን አለአግባብ መጠቀም በአውስትራሊያ ሕገወጥ ነው።

## ለአውስትራሊያ ታማኝነት

የኣውስትራሊያ ዜጎች ዜግነት በሚቀበሉበት ጊዜ ለኣውስትራሊያና ለህዝቧ ያላቸውን ታማኝነት ቃል ይገባሉ። የኣውስትራሊያ ዜጎች ሌላው ሃገር እስከፈቀደላቸው ጊዜ ድረስ ተጨማሪ ዜግነት ሊኖራቸው ይችላል። ይህም ባለ ብዙ ወይም ጥምር ዜግነት ይባላል። ይሁን እና አንድ ግለሰብ የሌላ ሀገር ዜግነት ቢኖረውም የአውስትራሊያ ዜጋ በአውስትራሊያ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ሁሉንም የአውስትራሊያን የሕጎች መከተል አለበት። የአውስትራሊያ ዜጎች ከሀገር ውጭ ቢሆኑም እንኳን ጥቂት የአውስትራሊያ ሕጎችን የግድ መከተል አለባቸው። ለምሳሌ በአውስትራሊያም ሆነ ከአውስትራሊያ ውጭ እድሜአቸው ከ16 ዓመት በታች ከሆኑ ሕፃናት ጋር የግብረ-ስጋ ግንኙነት መፈፀምም ሆነ በዚህ ተግባር ላይ መሳተፍ ለአውስትራሊያዊያን ሕገወጥነት ነው።

የኣውስትራሊያ ጥቅምና ደህንነት ለመጠበቅና ችላ ላለማለት የሁሉም የኣውስትራሊያዊ ግዴታ ነው። ለምሳሌ ኣንድን የመንግስት ምስጢር በማህበራዊ ሚድያ መለጠፍ የኣውስትራሊያን ጥቅም ኣሳልፎ መስጠት ነው። በተመሳሳይ ተለያዩ የጎሳ ማህበረሰቦች ኣለመተማመንና መፈራራት እንዲኖር ማደፋፈር የኣውስትራሊያ ማህበረሰብ ግንኙነት የሚጎዳ ነገር ነው።

በአውስትራሊያ ቀውስ/ አስጊ ሁኔታ ሲፈጠር ሕብረት እንፈጥራለን፤ እርስ በእርሳችን በክፉም በደጉም ጊዜ እንተጋገዛለን። በ2019-20 በአውስትራሊያ በነበረው ኃይለኛ የሰደድ እሳት የሕይወት፣ የንብረት፣ የዱር እንስሳት እና የከባቢ ምህዳር ውድመት ምክንያት፤ በሰደድ እሳቱ የተጎዱትን ሰዎችን ለመርዳት ሲባል ብዙ የተለያዩ ማሕበረሰቦች የገንዘብ፣ የአልባሳት እና የምግብ ድጋፍ አሰባስበዋል። ለምሳሌ በቪክቶሪያ የሚገኙ የቻይና የቬትናም እና የካምቦዲያ ማሕበረሰብ አባላት በገበያ ማዕከላት እርዳታ አሰባስቧል፣ በማሕበረሰብ አቀፍ ዝግጅቶች አማካኝነት ደግሞ የገንዘብ መዋጮ አሰባስበዋል። የሲክ ማሕበረሰብ በሺ የሚቆጠሩ የውሃ ጠርሙሶች በኩንስላንድ ለሚገኙ ማሕበረሰቦች እና የእሳት አደጋ ሠራተኞች አበርክተዋል።



# ለማጠቃለል

ዲሞክራሲያዊ ተቋሞቻችንና የጋራ እሴቶቻችን ኣውስትራሊያ ሰላማዊና የተረጋጋ ማህበረሰብ እንዲኖራት ኣድርገዋታል።

ሃብታምና ልዩ የሆነ የጋራ ባህል ኣለን። እንደ ኣውስትራሊያ ዜጋ የሃገራችን ታሪክ ሰሪና ለመፃኢ እድሏም ኣስተዋፅኦ ከሚያበረክቱ ኣካላት ወገን ይሆናሉ። ኣውስትራሊያ እጇን ዘርግታ ትቀበልዎታለች። ዜግነት የጋራ ማስተሳሰሪያችን ነው።

# ፈተና ለሚወጣባቸው ክፍሎች የሚረዳ የቃላት መፍቻ

### ስለ ኣቦርጅኖችና በቶረስ የባህር ወሽመጥ ደሴተኛ ህዝቦች/Aboriginal and Torres Strait Islander peoples/

ኣቦሪጂኖችና ቶረስ የባህረ ሰላጤ ደሴተኛ ህዝቦች ቀደምት የኣውስትራሊያ ነዋሪዎች ናቸው
*የኣውስትራሊያ ኣቦሪጂኖችና ቶረስ የባህረ ሰላጤ ደሴተኛ ህዝቦች የኣውስትራሊያ ህዝብ ሶስት በመቶ ያህል ይሸፍናሉ።*

### የአውስትራሊያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን

መድልዎ እና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ቅሬታን የሚመረምር ራሱን የቻለ ኮሚሽን ነው።
*የዘረኝነት ግጭቶች ለአውስትራሊያው የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ሊቀርብ ይችላል።*

### የኣውስትራሊያ የህዝብ ኣገልግሎት

የመንግስት መምሪያዎችና በነሱ የተቀጠሩ ሰዎች
*ፖል በአውስትራሊያው የማሕበረሰብ አገልግሎት ሥራ እንደ የአውስትራሊያ አገልግሎት ሠራተኛ ሆኖ ተቀጥራል።*

### የህዝብ ኣለመረጋጋት

የመንግስት ውሳኔ ወይም ፖሊሲ በመቃወም ብዙ ሰዎች ለሰላማዊ ሰልፍና ዓመጽ ይወጣሉ
*በህዝብ ተቀባይነት የሌለው ህግ በወጣ ጊዜ የህዝብ ዓመፅ ነበር።*

### ህብረት

መንግስት ወይም ጠንካራ የመንግስት ተፎካካሪ ለመሆን ሲባል የሚደረግ የሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ትብብር ነው
*ከምርጫ በኋላ በህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ውስጥ በኣብላጫ ድምፅ ኣሸናፊ የሆነ ፓርቲ ከሌለ ሁለት ተቀራራቢ ሃሳብ ያላቸው ተባብረው መንግስት ይሰራሉ።*

### ኮሚሽን

ህጋዊ ሃላፊነት ያላቸው የሰዎች ስብስብ
*የራሱ ነፃነት ያለው ኮሚሽን ምርጫውን ያካሂዳል።*

### ህገ መንግስት

የህጎች ሁሉ ህግ የሆነና የኣውስትራሊያ መንግስት መታዘዝ ያለበት
*ህገ መንግስቱ ህግ ኣውጪ፣ ህግ ኣስፈፃሚውና ህግ ተርጓሚ ኣካላትን ያዋቅራል።*

### ህገ መንግስታዊ ንጉሳዊ ስርዓት

በህገ መንግስቱ የተወሰነ ስልጣን የሚሰጥ በንጉስ ወይም መንግስት የሚመራ ኣገር።
*ህገ መንግስታችን የተቋቋመው በኣውስትራሊያ የጋራ ብልፅግና ህገ መንግስታዊ ንጉሳዊ ስርዓት ሆኖ የዩናይትድ ኪንግዶም ንጉስ ወይም ንግስት እንደ ርእሰ ብሄር የሚያስቀምጥ ነው።*

### ፍርድ ቤት

በዳኛ ወይም በኣጥቢያ ዳኛ ፊት የህግ ጉዳዮች የሚታይበት መድረክ ነው
*ሰዎች ህግ ሲጥሱ ወደ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ።*

### የወንጀል ክርክር

ኣንድ ሰው ጥፋተኛ መሆን ኣለመሆኑ በፍርድ ቤት ለመወሰን የሚሰማ የእውነታ ማጣራት ሂደት
*ከወንጀል ማጣራት ሂደት በኋላ የባንክ ዘራፊው ወደ እስር ቤት ተላከ።*

### የኮፒዩተር ዓለምን አለአግባብ መጠቀም

ሰውን ለመጉዳት ሆን ተብሎ የሚፈፀም ዛቻ፣ ማስፈራራት እና ጫና የሚፈጥር፣ የሚያዋርድ የበይነመረብ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም መጥፎ ስነምግባር ነው።
*የተለያየ ዓይነት የኮፒውተር ዓለም ንጥቃቶችን በመፈፀም በአውስትራሊያ ሕገወጥነት ነው።ይህ ለፖሊስ እና ለበይነመረብ አገልግሎት ለምሳሌ በአካባቢ ላለው ማሕበራዊ የመገናኛ ዘዴ ማሳወቅ ያስፈልጋል።*

ዲሞክራሲ/ህዝባዊ ስርዓተ መንግስት

በህዝብ በተመረጡ ተወካዮች ኣማካኝነት የሚቋቋም መንግስት

*ግሬስ ራሷ ድምፅ ሰጥታ በምትመርጣቸው ትወካዮቿ ኣማካኝነት የምትተዳደርበት ዲሞክራሲያዊ ሃገር ውስጥ መኖሯ ደስተኛ ናት።*

የቤትና ውስጥ እና የቤተሰብ ሁከት/ጥቃት

የትዳር አጋርን ለመቆጣጠር ሲባል የሚፈፀም የማስፈራራት ወይም ደህንነታቸውን ስጋት ላይ የመጣል ባህርይ ወይም ወይም የማስፈራራት ድርጊት ማለት ነው። የቤት ውስጥ እና የቤተሰብ ሁከትና ጥቃት ተቀባይነት የለውም፤ ሕገወጥም ነው።

*የቤት ውስጥ እና የቤተሰብ ሁከት በአውስትራሊያ ሕገወጥ ሲሆን ለፖሊስም ማሳወቅ ይገባል።*

የኣደንዛዥ እፅ ማስተላለፍ

ለሽያጭ በማሰብ ኣደንዛዥ እፅ መግዛት ወይም ይዞ መገኘት

*ጀስ በእፅ ኣስተላላፊነት ወንጀል ወደ እስር ተላከች።*

ምርጫ

ዜጎች በፓርላማ የሚወክሏቸውን ሰዎች የሚመርጡበት ሂደት ነው

*እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ የኣውስትራሊያ ዜጎች በምርጫ ወቅት የግድ ድምፅ መስጠት ኣለባቸው።*

የምርጫ መዝገብ

ሰዎች ለምርጫ ወይም ለሪፈረንደም የተመዘገቡበት ዝርዝር

*ጄን በድምፅ መስጫ ጣቢያ በደረሰችበት ወቅት የምርጫ ጣቢያ ሰራተኛው በምርጫ መዝገቡ ላይ ስሟን ፈለገው።*

የምርጫ ክልል

ፖለቲከኞች ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚመረጥባቸው ወረዳዎች

*የምርጫ ክልሎች፤ የምርጫ ወረዳዎች፣ዲቪዥኖች ወይም መቀመጫዎችም ይባላሉ።*

እኩልነት

በክብርና በደረጃ እኩል መሆን

*ኣውስትራሊያውያን በሰዎች እኩልነት ያምናሉ።*

ህግ ማስከበር

ሰዎች ህጉን ማክበራቸውን ማረጋገጥ

*ፖሊስ ህግ ያስከብራል ሰላምንም ያስጠብቃል።*

የህግ ኣስፈፃሚው ስልጣን

ህጉን ለማስፈፀም የተሰጠ ስልጣን፤ በኣውስትራሊያ ህገ መንግስት ካሉት ሶስት ስልጣናት ኣንዱ

*የኣውስትራሊያ ሚንስትሮችና ጠቅላይ ገዢው በኣውስትራሊያ ፓርላማ የወጣውን ህግ የማስፈፀም ስልጣን ኣላቸው።*

ፍትሃዊነት /እኩል ተጠቃሚነት

ማንኛውም ሰው ኣለምንም የኋላ ታሪክ ልዩነት ስኬታማ ህይወት እንዲኖረው እኩል እድል ይሰጠዋል

*በኣውስትራሊያ ሁሉም ሰው እኩል የተጠቃሚነት ዕድል ለሰጠው ይገባል ብለን እናምናለን።*

ፌደሬሽን

የተለያዩ የቅኝ ግዛቶች ተባብረው ኣንድ ሃገር የሆኑበትና እያንዳንዱ ቅኝ የተወሰነ ስልጣን ኣለው

*በ 1901 የቅኝ ግዛቶቹ ተዋህደው ሃገረቷም የኣውስትራሊያ የጋራ ብልፅግና ፌዴሪሽን ተባለች።*

የመጀመሪያዎቹ መርከቦች

በኒው ሳውዝ ዌልስ እስረኞችን ለማስፈር በካፒቴን ኣርተር ፊሊፕ ተመርተው ከብሪታንያ የመጡ 11 መርከቦች።

*የመጀመሪያዋ መርከብ ሲድኒ ኮቭ በተባለ የባህር ሰርጥ ጥር26 1788 ኣረፈች።*

የኣበባ ኣርማ

ብሄራዊ ኣበባ

*የኣውስትራሊያ የኣበባ ኣርማ ወርቃማው ዋትል ነው።*

የጉልበት ጋብቻ

ሁለቱም ወይም ከሁለት ኣንዱ ተጋቢ ያልተስማማበት ጋብቻ

*በጉልበት ጋብቻው ፈፅሞ ደስተኛ ስላልነበረች ሁሌም ትታ መሄድ ትፈልግ ነበር።*

### ከዚህ ጊዜ ጀምሮ

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለወደፊት
*በኣውስትራሊያ የዜግነት ስነስርዓት ላይ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለወደፊት ለኣውስትራሊያ ታማኝ ለመሆን ቃል ገብተሃል።*

### ድንቅ

በጣም ታዋቂ ምስል
*ኦፔራ ሃውስ የሲድኒ ድንቅ ምልክት ነው።*

### ተወላጅ/ሃገር በቀል

የአውስትራሊያው የአቦሪጂናል እና/ወይም ቶርስ የባሕር ወሽመጥ ደሴት ሕዝቦች
*የሃገሪቱ የመጀመሪያ ሰዎች የኣውስትራሊያ ቀደምት ተወላጆች ናቸው።*

### መዋሃድ

ስደተኞች እየተሻሻለች ባለችው ሃገር ለምደው እንዲሳተፉና የራሳቸውን ኣስተዋፅኦ የሚያደርጉበት ሂደት ነው
*በጊዜ ሂደት ስደተኞች ከኣውስትራሊያና ከኣካባቢው ህብረተሰብ ራሳቸውን ሲያዋህዱ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ።*

### የህግ ተርጓሚው ስልጣን

ህጎችን የመተርጎምና ተግባራዊ የማድረግ ስልጣን በአውስትራሊያ ህገ መንግሥት ስር ካሉት ሶስት ስልጣኖች አንደኛው ነው
*የአውስትራሊያ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን አላቸው።*

### የህግ አውጭነት ስልጣን

ህጎችን የማውጣትና የማሻሻል ስልጣን በአውስትራሊያ ህገ መንግሥት ስር ካሉት ሶስት ስልጣኖች አንደኛው ነው
*በህገ መንግሥቱ መሰረት ፓርያመንት ህጎችን ለማውጣት ስልጣን ይኖረዋል።*

### ነፃነት

የግል ነጻነት
*ዲሞክራሲያዊ በሆነው ሕብረተሰባችን ውስጥ ሰዎች የመናገር፣ የእራሳቸውን ሃሳብ የመግለጽ፣ በሃይማኖትና በማሕበር የመሰባሰብ ነጻነት አላቸው። ለነዚህ መብት ነጻነቶች ዋጋ ክብር እንሰጣለን። እነዚህን ነፃነቶችን እናከብራቸዋለን።*

### አጥቢያ ዳኛ

በዝቅተኛ ደረጃ ላለ ፍርድ ቤት ዳኛ
*የአጥቢያ ዳኛው ዘራፊውን ጥፋተኛ ሆኖ ስላገኘው ወደ እስር ቤት ላከው።*

### ጓደኝነት

በተለይ በችግር ጊዜ መረዳዳት ማለት እርዳታ መቀበልና ለሌሎች መስጠት
*መኪናዎ በሚበላሽበት ጊዜ ታዲያ መኪናዋን በመግፋት ሌላው ሹፌር በጓደኝነት መንፈስ ይረዳኛል።*

### የብሄራዊ መዝሙር

ብሄራዊ መዝሙር
*የአውስትራሊያ ብሄራዊ መዝሙር 'ኣውስትራሊያ በፍትሃዊነት እደጊ /Advance Australia Fair' ይባላል።*

### በፓርላማ ህዝባዊ ዲሞክራሲ አስተዳደር

በመደበኛ ምርጫ ጊዜ በዜጎች ለፓርላማ ተወካይነት የመምረጥ መንግሥታዊ አሰራር ዘዴ
*በፓርላማ ህዝባዊ አስተዳደር ሰዎች ድምጽ በመስጠት የራሳቸውን ተወካይ ይመርጣሉ።*

### የፖለቲካ ፓርቲ

ስለ አገሪቷ አስተዳደርና እንዴት መሆን እንዳለበት ተመሳሳይ ሀሳብ ያላቸው ሰዎች ስብስብ ሲሆን ብዙ ጊዜ መመረጥን ይፈልጋሉ
*የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ብዙጊዜ ይሰበሰባሉ፤ ለምሳሌ፡ ስለ የህዝብ ማጓጓዣ ማሻሻል ጉዳይ ለመነጋገር ይሆናል።*

### ዘረኝነት

በሰው ላይ በዘር፣ ቀለም፣ ትውልድ አገሩ ወይም ጎሳውን አስመልክቶ ተፅእኖ፣ መድልዎ፣ ጥቃት ወይም ጥላቻ ማሳደር ማለት ነው።
*ዘረኝነት በአውስትራሊያ ሕገወጥ ሲሆን በሚፈፀምበት ጊዜ ለፖሊስም ማሳወቅ ይገባል። ለአውስትራሊያው ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ቅሬታ ማቅረብ ይቻላል።*

### ህዝበ-ውሳኔ/referendum

በአውስትራሊያ ህገ መንግሥት ላይ ስለታቀደው ለውጥ በሁሉም መራጮች የሚሰጥ ድምጽ
*በ1967 ዓ.ም ውስጥ በተደረገው የህዝብ ውሳኔ ላይ በድምጽ መስጫ ቆጠራ ላይ የአውስትራሊያ ተወላጅ ህዝብ ድምጽ ተቆጥሯል።*

### ተወካይ

ሌሎችን ወክሎ የሚሰራ ወይም የሚናገር ሰው
*ያለኝን ሀሳብ የአካባቢየ ምክር ቤት ተወካይ ስለወደደው በምክር ቤት ስብሰባ ላይ አቅርቦታል።*

### ክብር

ሰዎች ለሚሰጡት ውሳኔ ውሳኔ እንደ ኣንድ ሰው ዋጋ ስጥ።
*ኤሚሊ ወላጆቿ ቡዲሂስት ለመሆን የወሰነችውን ውሳኔ ስላከበሩላት ደስተኛ ናት።*

### የህግ የበላይነት

ሁሉም ሰዎች ዜጎችና መንግስትን ጨምሮ የህግ ተገዢ ናቸው
*በኣውስትራሊያ ማንኛውም ሰው ጠቅላይ ሚንስተሩን ጨምሮ በህግ የበላይነት መሰረት ሁሉም ለኣውስትራሊያ ህግ ተገዢ ነው።*

### አገልግሎቶች በአውስትራሊያ

በመዲኬር፣ ስንተርሊንክ እና የሕፃናት ድጋፍ ሰጪ አማካኝነት የተለያዩ የጤና፣ ማሕበራዊ እና የበጎ አድራጎት ክፍያ እና አገልግሎት የሚሠጥ የአውስትራሊያ መንግስታዊ ድርጅት ነው።
*አገልግሎቶች በአውስትራሊያ በስንተርሊንክ እና በሌሎች አገልግሎቶች አማካኝነት የድጋፍ ክፍያዎችን ይፈፅማል።*

### የምስጢር ሳጥን

ሰዎች ኣለምንም ጫናን ተፅእኖ ሳይደርስባቸው በምስጢር ድምፃቸው የሚሰጡበት ስርዓት ነው
*በምስጢር የምርጫ ሳጥን ላይ ሆነው ድምፅዎን ለመስጠት በሚፅፉበት ጊዜ ማንም ሰው ሊያይዎት ኣይችልም።*

### ዓለማዊ

ከሃይማኖት የተለየ
*በዓለማዊ ማህበረሰብ መንግስታዊ ሃይማኖትየለም።*

### ራስን መቻል

ከሌላ ሰው እርዳታ ሳይፈልጉ የራስዎን ፍላጎት ማርካት
*ኣንድ ሰው ስራ እየሰራ ነው ማለት ምግቡንና የቤት ኪራዩን በራሱ መሸፈን ይችላል ማለት ነው። እሱ ራሱን የቻለ ነበር።*

### መመስረት

መገንባት፣ መመስረት፣መጀመር
*የመጀመሪያውን የኒው ሳውዝ ዌልስ ቅኝ ግዛት የመሰረቱት ፊሊፕ የሚባሉት ገዢ ናቸው።*

### ወረዳ

ኣካባቢያዊ የመንግስት ኣስተዳደር
*በኔ ወረዳ ያሉት መንገዶች ደህንነታቸው የተጠበቁ ናቸው።*

### ማህበራዊ ዋስትና

የመንግስት ጡረታ ወይም ስራ ለሌላቸው፣ የኣካል ጉዳት ለደረሰባቸው፣ለኣረጋውያንና ችግር ላይ ላሉ ለሌሎች ሰዎች የሚከፈል ክፍያ ነው
*ትራንግ ስራዋን ካጣች በኋላ ለማህበራዊ ዋስትና ክፍያ ኣመልክታለች።*

### የአውስትራሊያ የግብር መስሪያ ቤት(ATO)

የኣውስትራሊያውያን የገንዘብ ኣገልግሎቶችን የሚያግዝ፣ የግብር እና ጡረታ ስርዓትን የሚከታተል የኣውስትራሊያ መንግስታዊ ተቋም ነው።
*አብዛኛው አውስትራሊያዊን ለአውስትራሊያው የግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት በየአመቱ ግብር ይከፍላሉ።*

### እሴቶች

ኣንድ ሰው ስለ ማንኛውም ነገር ትክክል ወይም ስህተት ነው ብሎ የሚወስንበትና በተለያዩ ሁኔታዎች የሚተገበርበት መመሪያ ነው
*የኣውስትራሊያ እሴቶች የሚባሉ ኣውስትራሊያ የምትጋራቸው የጋራ እሴቶች ኣሉ።*

### የበጎ ፈቃደኝነት

ኣንድ ሰው ኣለምንም ክፍያ ለኣንድ ሰው ወይም ለኣንድ ድርጅት የሚሰጠው ጊዜ ነው
*ራዛ በቤቱ ለሰዎች በነፃ እንግሊዝኛ የሚያስተምር በጎ ፈቃደኛ ነው።*



# ፈተና የሚደረግበት ክፍል ኣልቋል